የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ፰ኑሜ ፫ ቀን ፪ሺ፲፰ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No.58
ADDIS ABABA, 8th September, 2026

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፫/፪ሺ፲፰
የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አዋጅ.....
.....ገጽ ፳ሺ፩፻፲፭

Content

Proclamation No. 1433/2026
Agribusiness Company Proclamation
.....Page 20115

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፫/፪ሺ፲፰

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አዋጅ

ግብርና የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የኢንዱስትሪ ልማት እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ዋነኛ መሠረት መሆኑን በመገንዘብ፣ ኋላቀር ከሆነው የግብርና አሠራር በመላቀቅ ወደ ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪ እና ገበያ መር ሥርዓት መሸጋገር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮችን በግብርና ቢዝነስ ኩባንያ በማደራጀትና በማቀናጀት ምርታማነትን ማሳልበት፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስፈን በማስፈለጉ፣

የአነስተኛ ይዞታ አምራቾችን የቢዝነስ እሳቤ በማስፋት ምርት የማሰባሰብ፣ እሴት የመጨመር እና በገበያ የመደራደር አቅማቸውን በማሳደግ ለምርቶቻቸው ተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ በማድረግ ወደ መካከለኛ አልሚነት ለማሸጋገር የሚያስችል አማራጭ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

PROCLAMATION NO 1433/2026

AGRIBUSINESS COMPANY PROCLAMATION

WHEREAS, realizing that agriculture is a foundation for Ethiopia's economic growth, industrial development and job creation; and, as such, it is necessary to transition from the traditional agricultural practices to a modern, competitive, and market-oriented system;

WHEREAS, it is crucial to organize and integrate smallholder farmers, pastoralists, and agro-pastoralists into agribusiness companies in order to enhance productivity, ensure food security and achieve inclusive economic growth;

WHEREAS, it is necessary to create an alternative institutional organization that enables widening the business mindset of smallholder producers and enhancing their capacity for product aggregation, value addition and market negotiation with the view to securing a commensurate price for their products and ultimately facilitating their transition into medium scale investors;

የአነስተኛ ይዞታ አምራቾችን በኩባንያ በማደራጀት፣ ባላቸው የመሬት ይዞታ፣ የእንሰሳት ሃብታቸውን እና ጉልበታቸውን ወደ ካፒታል በመለወጥ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቸውን ለማሳደግ የሚያስችል ግልጽ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ሕግ ባለመደንገጉ የዘርፉን ዕድገት የሚያሳልጥ ምቹ የሆነ ግልጽ አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፫/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"አርሶ አደር"** ማለት የራሱ በሆነ ሕጋዊ የመሬት ይዞታ ወይም በኪራይ ባገኘው መሬት ላይ በዋናነት ሰብል የማምረት ስራ ላይ ተሰማርቶ እራሱንና ቤተሰቡን የሚያስተዳድር የተፈጥሮ ሰው ነው፤

፪/ **"አርብቶ አደር"** ማለት በዋናነት በእንስሳት እርባታ እራሱን እና ቤተሰቡን የሚያስተዳድር የተፈጥሮ ሰው ነው፤

፫/ **"ከፊል አርብቶ አደር"** ማለት የራሱ በሆነ ሕጋዊ የመሬት ይዞታ ወይም በኪራይ ባገኘው መሬት ላይ ሰብል ማምረትን እና የእንስሳት እርባታን እንደ ዋና መተዳደሪያ አድርጎ እራሱን እና ቤተሰቡን ለማስተዳደር የሚጠቀም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

WHEREAS no clear agricultural business company law has been enacted to enable smallholder producers to organize themselves into companies and, by converting their land holdings, livestock assets, and labor into capital, to enhance their economic benefits; and to establish a clear and conducive framework that facilitates the development of the sector;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

SECTION ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Agribusiness Company Proclamation No. 1433/2026".

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Farmer"** means a natural person who is engaged mainly in crop production on his own legal landholding or on land obtained through rent to sustain himself and his family;

2/ "**Pastoralist**" means a natural person who sustains himself and his family mainly through animal production ;

3/ **"Agro-pastoralist"** means a natural person who is engaged mainly in both crop and livestock production on his own legal landholding or on land obtained through rent to sustain himself and his family;

፬/ **"እንስሳት"** ማለት ሰውን ሳይጨምር ማንኛውንም አከርካሪ አጥንት ያላቸው አጥቢዎች፣ አዕዋፍ፣ ወይም የውሃ ውስጥ እንስሳት ሲሆኑ ንብንና የሐር ትልን ጨምሮ ሌሎች አከርካሪ የሌላቸውንም ይጨምራል፤

4/ **"Animal"** means any vertebrate mammal, excluding humans, and includes bird, aquatic animals, and other invertebrates, such as bees and silkworms;

፭/ **"ድርጅት"** ማለት የአነስተኛ ይዞታ አምራች ሆነው በጎብረት ስራ ማህበር ወይም በአነስተና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የተደራጁ አካላትን የሚመለከት ነው፤

5/ **"Organization"** means an entity or group of smallholder producers organized as a cooperative society or as a micro and small enterprise;

፮/ **"አምራች"** ማለት ዓመታዊ ወይም ቋሚ ሰብሎች የማምረት፣ እንስሳትን የማርባት ወይም በሁለቱም ተግባራት ላይ የተሰማራ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ወይም ድርጅት ነው፤

6/ "**Producer**" means a farmer, pastoralist, agro-pastoralist or an organization engaged in the production of annual or perennial crops, animal production or both activities;

፯/ **"አነስተኛ ይዞታ"** ማለት መጠኑ እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያይ የሚችል ሆኖ ኑሮው በዋናነት በግብርና ላይ የተመሠረተ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ራሱንና ቤተሰቡን ለማስተዳዳር በይዞታነት የያዘው የመሬት ወይም የእንስሳት መጠን ነው፤

7/ **"Smallholding"** means a size of land or livestock held by a farmer, pastoralist, or agro-pastoralist, mainly dependent on agriculture or the purpose of sustaining himself and his family, the size of which may vary according to the context of the regions;

፰/ **"ግብርና ቢዝነስ"** ማለት የግብርና ግብዓትን ማምረትና ማቅረብን፣ የግብርና ምርቶችን ማምረትን፣ ምርት ማከማቸትን፣ ማጓጓዝን፣ ማቀነባበርን፣ ግብይትን፣ ምርት ማከፋፈልን ወይም ተያያዥ የግብርና ልማት ሥራዎችን ያካትታል፤

8/ "**Agribusiness**" means the production and supply of agricultural inputs, as well as the production, storage, transportation, processing, marketing and distribution of agricultural produces, and includes other related agricultural activities;

፱/ **"ክላስተር"** ማለት በአንድ አካባቢ በተመሳሳይ የግብርና ምርት ዓይነቶች ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ የሰብል ምርት በአጎራባች ገጠም ማምረትን ወይም በአንድ መንደር በአሰፋፊር ተቀራራቢ በሆኑ አነስተኛ ይዞታ አምራቾች የሚካሄድ እንስሳት እርባታን የሚያካትት የአመራረት ዘዴ ነው፤

9/ "**Cluster**" means a method of production that includes the producing crop on adjoining farmlands to enhance productivity and competitiveness of similar agricultural commodities in an area or animal production in a village by smallholder producers settling close to each other;

፲/ "**አደራጅ ኮሚቴ**" ማለት በሚኒሰቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን እውቅና የሚቋቋም ሆኖ የአነስተኛ ይዞታ አምራች ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ድርጅቶች በግብርና ቢዝነስ ኩባንያ እንዲደራጁ የሚያሳምን እና የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ማቋቋምን ዓላማው አድርጎ የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው፤

10/ "**Organizing Committee**" means a group that is established with the approval of the Ministry or appropriate authority, and engaged in convincing smallholder producer individuals, groups or organizations to be organized into agribusiness companies, and operates with the purpose of establishing an agribusiness company;

፲፩/ "**የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ**" ማለት የአነስተኛ ይዞታ አምራቾች የቢዝነስ እሳቤያቸውን በማስፋት ምርት የማሰባሰብ፣ የማደራጀት እና በገበያ የመደራደር አቅማቸውን በማሳደግ፤ እንዲሁም የግብርና ምርትን በማቀነባበርና እሴትን በመጨመር ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ፣ ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ እና ወደ መካከለኛ አልሚነት እንዲሸጋገሩ ለማስቻል የሚቋቋም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋማዊ አደረጃጀት ነው፤

11/ "**Agribusiness Company**" means an institutional organization that has legal personality and established by smallholder producers, and enables them to widen their business mindset and enhance their capacity for product aggregation, organization and market negotiation, and to increase their income through agricultural products processing and value addition, and ultimately improving their livelihoods and transitioning into medium scale investors;

፲፪/ "**አማካሪ ቦርድ**" ማለት ለግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫን የሚያመለክት ወይም ሙያዊ ምክር የሚሰጥ አግባብነት ያለው የትምህርት ደረጃ እና የስራ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ያካተተ የኩባንያው አባል ያልሆኑ የአማካሪዎች ቡድን ነው፤

12/ **"Advisory Board"** means a group of advisors who are not members of the company, consisting of professionals who possess relevant educational qualifications and work experience and provide strategic direction or professional advice to an agribusiness company;

፲፫/ "**አባል**" ማለት በግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የመመስረቻ ጽሑፍ መሰረት የተደነገጉትን የአባልነት መስፈርቶች በማሟላት ለአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ሰው ነው፤

13/ "**Member**" means a person that has duly applied and been accepted for membership in an agribusiness company by fulfilling the criteria for membership as stipulated under the company memorandum of association;

፲፬/ **"ትርፍ"** ማለት አንድ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ በሂሳብ ዓመቱ ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ ጠቅላላ የኩባንያው ወጪዎች ተቀንሰው የሚቀረው ገንዘብ ነው፤

14/ "**Profit**" means the amount of money obtained after the total expenses of an agribusiness company are deducted from the company total revenue generated in a fiscal year;

፲፭/ **"የተጣራ ትርፍ"** ማለት አንድ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ በሂሳብ ዓመቱ ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ የኩባንያው ጠቅላላ ወጪዎች፣ ግብር፣ የአላቂ ንብረቶች መተኪያ ገንዘብ እና የእርጅና ቅናሽ ሂሳብ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ገንዘብ ነው፤

15/ "**Net Profit**" means the amount of money obtained after the total expenses of an agribusiness company, taxes, costs of depreciation and consumable assets are deducted from the company total revenue generated in a fiscal year;

፲፮/ **"የሚከፋፈል ትርፍ"** ማለት ከሂሳብ ዓመቱ የተጣራ ትርፍ ላይ የቀደምት ዓመታት ኪሳራዎች ከተቀነሱ በኋላ በፊት ታስበው ያልተከፋፈሉ ትርፎችን፣ ሌሎች ተጨማሪ ገቢዎችን እና በልዩ ሁኔታ ጠቅላላ ጉባኤው ከመጠባበቂያ ገንዘብ ላይ እንዲከፈል የፈቀደውን ማንኛውንም ገንዘብ በሂሳብ ዓመቱ የተጣራ ትርፍ ላይ በመጨመር የሚገኝ የኩባንያው ገንዘብ ነው፤

16/ "**Distributable Profit**" means the amount of money obtained after the losses in the previous years are deducted from the net profit in a fiscal year, and the company's profits previously calculated but remained undistributed, other additional incomes, and any additional fund specially authorized by the general assembly to be paid from reserve funds are added to the net profit in the fiscal year;

፲፯/ **"መዋሃድ"** ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች ውህደት በመፍጠር ኩባንያዎቹ ተቀላቅለው አንዱ ሌላውን ወይም ሌሎቹን በመዋጥ፣ አለያም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ኩባንያዎች አዲስ ኩባንያ በመመስረት ነባር ኩባንያዎቹ በአዲሱ ኩባንያ ውስጥ የሚጠቃለሉበት ሁኔታ ነው፤

17/ **"Merger"** means a condition where two or more agribusiness companies merge into one either by one of them acquiring the rest or two or more agribusiness companies forming a new company and merging into the new one;

፲፰/ **"መከፈል"** ማለት የአንድ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ሙሉ ንብረት እና እዳዎች ከአንድ በላይ ለሆኑ ነባር ወይም አዲስ ለሚመሠረቱ ኩባንያዎች በማከፋፈል የሚከፈለው ኩባንያ የሚከስምበት ሁኔታ ነው፤

18/ **"Division"** means a condition in which the entire assets and liabilities of an agribusiness company are distributed among two or more existing or newly established companies, resulting in the dissolution of the company being divided.;

፲፱/ **"ሚኒስቴር" ማለት ግብርና ሚኒስቴር ነው፤**

፳/ **"ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማን እና ድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤**

፳፩/ **"አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት በክልል ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው የመንግስት ተቋም ነው፤**

፳፪/ **"ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤**

፳፫/ *ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።*

19/ "**Ministry**" means the Ministry of Agriculture;

20/ "**Region**" means any of the regions constituted in accordance with Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and includes the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administration;

21/ "**Appropriate Authority**" means a government institution authorized by a Region to implement this Proclamation;

22/ "**Person**" means any natural or juridical person;

23/ Any expression in the masculine gender shall also include the feminine.

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በመላ ሃገሪቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall be applicable throughout the country.

፬. <u>የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ዓላማዎች</u>

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ **የአነስተኛ ይዞታ አምራቾችን የአደራጃጀት ሥርዓት በመገንባት ወደ መካከለኛ አልሚነት በመሻገር ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ ማስቻል፤ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ማዘመን እና ለገጠር ትራንስፎርሜሽን እውን መሆን አስተዋጽኦ ማድረግ፤**

፪/ **የግብርና ግብዓትና ቴክኖሎጂ አቅርቦትን በማሳለጥ እና ተደራሽ በማድረግ የአነስተኛ ይዞታ አምራቾችን ምርት፣ ምርታማነት እና ገቢ ማሳደግ፤**

4. <u>Objectives of an Agribusiness Company</u>

An Agribusiness company shall have the following objectives:

1/ Building an organizational system for smallholder producers to transition into medium scale developers, improve their livelihoods, modernize the agricultural sector, and contribute to the realization of rural transformation;

2/ Enhancing the production, productivity and income of smallholder producers by facilitating the supply and accessibility of agricultural inputs and technology;

፫/ የግብርና ምርትን በከፍተኛ መጠንና ጥራት በማሰባሰብ፣ የግብይትና እሴት ጭመራ ተግባራትን በማዘመንና ውጤታማ በማድረግ የአነስተኛ ይዞታ አምራቾችን ኑሮ ማሻሻልና ለኢኮኖሚው አድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል፤

፬/ ለአነስተኛ ይዞታ አምራቾች የፋይናንስ እና የኢንሹራንስ ተደራሽነትን በማመቻቸት ከአግልግሎቱ ተጠቀሚ ማድረግ፤

፭/ የግብርና ግብይት እና የገጠር መሰረተ ልማቶችን ማስፋፋት እና የገጠርና የከተማ እንዲሁም የግብርናና የኢንዱስትሪ ትስስር ማጠናከር፤

፮/ የአነስተኛ ይዞታ አምራቾችን አቅም በሁሉም ደረጃ በማጎልበት የእውቀት፣ የክህሎት እና የመደራደር አቅማቸውን ማሳደግ።

3/ Improving the livelihoods of smallholder producers and enabling them to contribute to the economic growth through aggregation of agricultural products in large quantity and quality, and modernization and improved effectiveness of marketing and value addition activities;

4/ Facilitating the accessibility of finance, insurance, and technology for smallholder producers to ensure their benefit from the services;

5/ Promoting agricultural marketing, expanding rural infrastructure, strengthening the linkages between rural and urban centers, and the agriculture and industry sectors;

6/ Enhancing the capacity of smallholder producers at all levels to improve their knowledge, skills and bargaining power.

፭. <u>የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ መሰረታዊ መርሆዎች</u>

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ መርሆዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

፩/ እኩልነት፤

፪/ ፍትሃዊነት፤

፫/ ዘላቂነት፤

፬/ ቅልጥፍና፤ ወጪ ቆጣቢነት፤

፭/ መተባበር፤

፮/ አካታችነት፤

፯/ ግልጽነትና፤ ተጠያቂነት፤

፰/ ጥራት፤

፱/ ታማኝነት።

5. <u>Fundamental Principles of Agribusiness Company</u>

The principles of an agribusiness company shall be the following:

1/ Equality;

2/ Justice;

3/ Sustainability;

4/ Efficiency and cost-effectiveness;

5/ Cooperation;

6/ Inclusiveness;

7/ Transparency and accountability.

8/ Quality;

9/ Loyality.

ክፍል ሁለት

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ምስረታ፣ ምዝገባ እና የስራ መስኮች

፮. የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አመሰራረት

፩/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የሚመሰረተው፡-

ሀ) በግብርና የስራ መስክ በተሰማሩ አነስተኛ ይዞታ አምራች ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ወይም የእነዚህ አካላት ጥምረት፤

ለ) በክላስተር የግብርና ስራ መስክ የተሰማራ ድርጅት ራሱን ወደ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ሲለውጥ፡፡

፪/ የኩባንያው መስራች አባላት ብዛት፡-

ሀ) በአዝርዕት ሰብሎች ከሆነ ቢያንስ ሦስት መቶ፤ ወይም

ለ) በአትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች ወይም በእንሰሳት እርባታ ከሆነ ቢያንስ አንድ መቶ ሃምሳ መሆን አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተመለከተው ያነሰ የመስራቾች ቁጥር ያለው የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ወይም በሌሎች የግብርና ምርት አይነቶች የሚቋቋምበትን ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የአካባቢ ነባራዊ ሁኔታዎችንና የኢኮኖሚ አዋጭነትን መሠረት በማድረግ በሚያካሂደው ጥናት መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

፬/ ማንኛውም የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የሚመሰረተው ከታወጀው የድርሻ መጠን ሃያ አምስት ከመቶ ሲከፈል ነው፡፡

፭/ በጥሬ ገንዘብ የተሸጡ ድርሻዎች ጠቅላላ ዋጋ ኩባንያው ከመመዝገቡ በፊት በመመስረት ላይ ባለው ኩባንያ ስም በተከፈተ ዝግ ሂሳብ መቀመጥ አለበት፡፡

SECTION TWO

FORMATION, REGISTRATION AND AREAS OF BUSINESS OF AN AGRIBUSINESS COMPANY

6. Formation of an Agribusiness Company

1/ An agribusiness company may be formed:

a) by smallholder producer individuals or organizations engaged in the agriculture sector, or a combination of these entities;

b) when an organization engaged in cluster farming converts itself into an agribusiness company.

2/ Founding members of an agribusiness company shall be:

a) at least Three Hundred members for crop farming;

b) at least One Hundred Fifty members for horticulture or animal production.

3/ An agricultural business company having less founders than the number specified under Sub-Article (2) of this Article, or a company to be established in other types of agricultural products, shall be implemented based on a study conducted by the Ministry or the Appropriate Authority, taking into account the existing local conditions and economic feasibility.

4/ Any agribusiness company shall be established after collecting payements for 25% of the declared share.

5/ The total value of shares sold in cash must be deposited in a block bank account opened in the name of the agribusiness company under formation before the company is registered.

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) እንደተጠበቀ ሆኖ ከአባልነት መመዘገቢያ የሚሰበሰበው ገንዘብ በአደራጅ ኮሚቴ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ገቢ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ለአስተዳደራዊ ወጪዎች እንዲውል ይደረጋል፡፡

6/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (5) of this Article, the money collected from the members as registration fee shall be deposited in a bank account opened in the name of the organizing committee and used to cover administrative costs as deemed necessary.

፯/ የድርሻ ክፍያ የተፈጸመው በዓይነት ከሆነ እንደንብረቱ ሁኔታ በመመስረት ላይ ባለው ኩባንያ ስም መመዝገቡንና የባለቤትነት ማስረጃ በኩባንያው ስም መዘጋጀቱን ማረጋገጥ እና አደራጅ ኮሚቴው በሚወስነው ቦታ መቀመጥ አለበት፡፡

7/ Where the value of shares is paid in kind, it must be ensured that it is registered in the name of the company under formation depending on the nature of the property, and that the title deed is prepared in the name of the company and deposited in a place designated by the organizing committee.

፰/ በክላስተር የግብርና ስራ መስክ የተሰማራ ድርጅት የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አባል በሚሆንበት ጊዜ በኩባንያው ውስጥ እንደ አንድ አባል ሆኖ ይቆጠራል፡፡

8/ When an organization engaged in cluster farming becomes a member of an agribusiness company, it shall be treated as a single member within the company.

፯. <u>የድርሻ ዋጋ እና የካፒታል መጠን</u>

7. <u>Value of Shares and Amount of Capital</u>

፩/ በግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ውስጥ የሁሉም ድርሻ ዋጋ እኩል መሆን አለበት፡፡

1/ The par-value of each share of an agribusiness company shall be equal.

፪/ የኩባንያው የአንድ ድርሻ ዋጋ ከአንድ ሺህ ብር በታች መሆን የለበትም፡፡

2/ The par-value of each share shall not be less than one thousand Birr.

፫/ የኩባንያው ዝቅተኛው የተከፈለ ዋና ካፒታል ከአንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

3/ The minimum paid capital of the company shall not be less than One Million Five Hundred Thousand Birr.

፬/ ጠቅላላ ጉባኤው የድርሻ ዋጋ ውጥ እንዲደረግ ሲወስን የድርሻ ዋጋ በየጊዜው ሊጨምር ችላል፡፡

4/ The value of share may increase over time when the General Assembly decides to make changes to the value of shares.

፭/ ኩባንያው የሚደራጅበት የግብርና ስራ ዘርፍ በዋናነት የአዝርዕት ሰብሎች ከሆነ አንድ አባል ሊገዛ የሚችለው ዝቅተኛው ድርሻ አምስት ሲሆን በአትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች ወይም በእንሰሳት

5/ Where the primary agricultural activity the company is engaged in is crop farming, the minimum number of shares a member can purchase is Five; and where the primary agricultural activity is

እርባታ ከሆነ ዝቅተኛው ድርሻ አስር መሆን ይኖርበታል፡፡

፮/ ማንኛውም አባል ኩባንያው ሲመሠረት ዝቅተኛውን የድርሻ መጠን ሙሉ በሙሉ መክፈል እና በተጨማሪ ሊገዛ ቃል ከገባው ድርሻ ውስጥ ቢያንስ አንድ አራተኛውን ከፍሎ ቀሪውን ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ክፍሎ መጨረስ አለበት፡፡

፯/ ማንኛውም የኩባንያው አባል በጠቅላላ ጉባኤ እንዲሸጥ ከተወሰነው የድርሻ መጠን አስራ አምስት በመቶ በላይ ድርሻ መግዛት አይችልም፡፡

፰/ በዓይነት የተከፈለ ድርሻ የአገማመት ዘዴ በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፰. <u>የአባልነት መስፈርት</u>

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አባል ለመሆን የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

፩/ ዕድሜው አስራ ስምንት ዓመት የሞላው፤

፪/ በሕግ ችሎታ የሌለው ሰው ከሆነ፤ በሕጋዊ ሞግዚት መወከል፤

፫/ የአነስተኛ ይዞታ አምራች መሆን፤

፬/ የኩባንያውን ዝቅተኛ ድርሻ መጠን መግዛት የሚችል፤

፭/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚወስነው መሰረት የመመዝገቢያ ክፍያ መክፈል የሚችል፤

፮/ የኩባንያውን ዓላማ የተቀበለና ተያያዥ ግዴታዎችን ለመወጣት ፈቃደኛ የሆነ፤ እና

horticulture or animal production, the minimum number of shares a member can purchase is ten.

6/ Every member should fully pay the value of the minimum share and at least one-fourth of any additional share the member pledged to buy at the beginning of the formation of the company and pay the remaining amount within Two years from the date of the formation of the company.

7/ No member shall hold more than Fifteen percent of the total number of shares decided to be sold by the General Assembly.

8/ The method for valuation of shares paid in kind shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry.

8. <u>Criteria for Membership</u>

The following criteria should be fulfilled in order to become a member of an agribusiness company:

1/ Has attained Eighteen years of age;

2/ Be represented by legal guardians, if legally incapable person

3/ Be a small holder producer;

4/ Be capable of purchasing the company's minimum number of shares;

5/ Be able to pay the registration fee in accordance with the decision of the Ministry or Appropriate Body;

6/ Has accepted the objectives of the company and be willing to fulfill the related obligations;

፯/ ይህንን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች የተወሰኑ ተጨማሪ መስፈርቶችን የሚያሟላ፡፡

7/ Fulfill the criteria specified in the Regulations and Directive issued for the implementation of this Proclamation.

፱. <u>አደራጅ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

9. <u>Establishing Organizing Committee</u>

፩/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አደራጅ ኮሚቴ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን እውቅና ይቋቋማል፡፡

1/ An Organizing Committee of an agribusiness company shall be established with the recognition of the Ministry or Appropriate Body.

፪/ ኮሚቴው ከአምስት ያላነሰ ከአስራ ሦስት ያልበለጠ አባላት ይኖሩታል፡፡

2/ The Committee shall have a minimum of Five and maximum of Thirteen members.

፫/ የኮሚቴው አባላት ከአነስተኛ ይዞታ አምራቾች ወይም ከሚቋቋመው ኩባንያ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ካላቸው የግሉ ዘርፍ ወይም በጥምር ሊሆን ይችላል፡፡

3/ Members of an organizing committee can be from smallholder producers or from private sector relevant to the objectives of agribusiness companies or a combination of these.

፲. <u>የአደራጅ ኮሚቴ አባልነት መስፈርት</u>

10. <u>Criteria for Membership of an Organizing Committee</u>

የኮሚቴው አባላት ከሚከተሉት ውስጥ ይሆናል፡-

The members of the Committee shall be from the following:

፩/ ከአነስተኛ ይዞታ አምራቾች፤

1/ Smallholder producers;

፪/ ከሚቋቋመው ኩባንያ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ካላቸው የግሉ ዘርፍ፤

2/ The private sector relevant to the objectives of the company being established;

፫/ በፍርድ መብቱ ያልታገደ ሰው ወይም ከዚህ በፊት በተመሰሳሳይ ስራ ወይም ኃላፊነት ላይ ጥፋት ያልፈፀመ ፤

3/ A person whose civil rights have not been suspended by a court of law or who has not committed an offense during a similar task or responsibility in the past;

፬/ ለአደራጅ ኮሚቴው የጥናት፣ የሙያ ድጋፍ ወይም መሰል አገልግሎት ያላቀረበ ባለሙያ፣ ቡድን ወይም ተቋም፤

4/ A professional, group, or institution that has not provided research, professional support or similar services to the organizing committee;

፭/ የመንግስት ተቋማት የአደራጅ ኮሚቴ አባል መሆን አይችሉም፡፡

5/ Government institutions may not be members of the Organizing Committee.

፲፩. የአደራጅ ኮሚቴ ተግባራት

አደራጅ ኮሚቴ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል፡-

፩/ አነስተኛ ይዞታ አምራቾች በግብርና ቢዝነስ ኩባንያ እንዲደራጁ የማስተባበር፣ የማሳመን፤ መግለጫ አዘጋጅቶ በኩባንያው አባል እንዲሆኑ የመጋበዝ እና የኩባንያ ምስረታን ዓላማ አድርጎ መስራት፤

፪/ የኩባንያው አባል ለመሆን የተመዘገቡት አባላት የገዙትን ድርሻ መክፈላቸውን እና በኩባንያው ስም ገንዘቡ ገቢ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፫/ በዓይነት የተከፈሉ ድርሻ በገንዘብ የተተመኑ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፬/ የኩባንያው አመሠራረት ሂደት ህጋዊ አሠራርን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

፲፪. ለአደራጅ ኮሚቴ ስለሚፈጸም ክፍያ እና ወጪዎች

፩/ አደራጅ ኮሚቴ በኩባንያው ምስረታ ሂደት ያወጣቸው ወጪዎች ለምስረታው አስፈላጊ መሆናቸው በኦዲተር ተረጋግጦ በጠቅላላ ጉባኤ መጽደቅ አለበት፤ ወጪው ለዚሁ ዓላማ ከተሰበሰበው ገንዘብ በላይ ከሆነ ከኩባንያው እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡

፪/ ኩባንያው በማንኛውም ምክንያት ሳይቋቋም ከቀረ የኩባንያውን ድርሻ የገዙ ሰዎች አደራጅ ኮሚቴው ላወጣቸው ወጪዎች ኃላፊነት የለባቸውም፡፡

11. Functions of Organizing Committee

An organizing committee shall perform the following functions:

1/ Promoting for smallhoder producers to be organized into agribusiness companies, inviting them to join the company, or operating with the purpose of establishing a company;

2/ Ensuring that those who have registered for membership of the company have paid the shares they purchased and the payment is deposited in the name of the company;

3/ Ensuring that the shares paid in kind are valued in terms of money;

4/ Ensuring that the process of the formation of the company complies with the legal procedures.

12. Remunerations and Expenses of Organizing Committee

1/ The expenses incurred by the organizing committee during the formation of company shall be verified by Auditor and approved by the General Assembly to ensure that the expenses were necessary for the formation of the company, and the expenses shall be reimbursed by the company if it is higher than the amount of money collected for this purpose.

2/ If the company is not established for whatsoever reason, those who have purchased shares are not liable for the expenses incurred by the organizing commite.

፫/ ለአደራጅ ኮሚቴ የሚፈጸም ክፍያን በተመለከተ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚወሰን ይሆናል።

3/ Issues regarding the remuneration for organizing committee shall be determined based on a Directive to be issued by the Ministry.

፲፫. ስለ መመስረቻ ጽሁፍ

13 Memorandum of Association

፩/ ማንኛውም የግብርና ቢዝነስ ኩባያን የሚቋቋመው በመመስረቻ ጽሁፍ ሆኖ የመመስረቻ ጽሁፍ ሞዴል በሚኒስቴሩ ሊዘጋጅ ይችላል።

1/ Every agribusiness company shall have a memorandum of association for its establishment, and a model of memorandum of association may be prepared by the Ministry.

፪/ የመመስረቻ ጽሁፉ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መያዝ ይኖርበታል፦

2/ The memorandum of association shall contain the following:

ሀ) የኩባንያው አባላት ስም፣ ዜግነት፣ አድራሻ፣ የአባልነት መስፈርት ስለማሟላታቸው የሚገልፅ ጽሁፍ፤

a) the name, nationality, address of the members of the company, and statement describing the fulfilment of membership criteria;

ለ) የኩባንያው ስያሜ፣ የተመሰረተበት ዘመን፣ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኝበት ቦታ፣ እንዲሁም ቅርንጫፎቹ፤

b) the name of the Company, date of establishment, the location of head office and branch offices;

ሐ) የኩባንያው ዓላማ፤

c) the objective of the Company;

መ) የኩባንያው ካፒታል እና የተከፈለ መጠን የሚያሳይ ማረጋገጫ፤

d) the capital of the Company and verification of the amount paid;

ሠ) እያንዳንዱ የኩባንያው አባል የያዘው የድርሻ ብዛት እና የከፈለው የገንዘብ መጠን፤

e) the number of shares held and amount paid by each member of the company;

ረ) በዓይነት የተከፈለ ድርሻ ከሆነ ግምቱን፤

f) valuation of the shares, if it is paid in kind;

ሰ) በኩባንያው ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ የእያንዳንዱ አባል ድምጽ የሚወሰነው በኩባንያው ባስመዘገበው የማምረቻ መሬት ስፋት እና በሚያቀርበው የምርት መጠን መሆኑን የሚገልፅ ጽሁፍ፤

g) a statement that the decision-making power of each member of the company is determined by the size of the land registered with the company and the amount of product the member supplies to the company;

ሸ) የአባልነት መስፈርቶች እና ከአባልነት መሰናበቻ ምክኒያቶች ዝርዝር፤

h) the detail criteria for membership, and causes for dismissal from membership;

ቀ) የኩባንያው ድርሻዎች ስለሚተላለፉበት የአሠራር ሁኔታ፤

i) the procedure for transfer of the shares of the company;

በ) የትርፍ ክፍፍል ሥርዓት፣

ተ) የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ብዛት፣ ተግባር እና ኃላፊነት፣ የስራ ዘመን እና ከኃላፊነት ስለሚነሱበት ሁኔታ፣

ቸ) የኩባንያው የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ብዛት፣ ተግባርና ኃላፊነት እና የስራ ዘመን፣

ኀ) የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነቶች፣ የተጠያቂነት ወሰን፣ የሚቀጠርበትና የሚሰናበትበት ሁኔታ፣

ነ) የኩባንያው የሥራ አፈፃፀም እና የኦዲት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርብበት ጊዜና መንገድ፣

ኘ) በኩባንያው ሥራ አመራርና በአባላት ወይም በአባላት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከቱ ጉዳዮች፣

አ) ሌሎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ባከበረ መልኩ የኩባንያው አባላት የደረሱባቸው ስምምነቶች።

j) the system for dividends;

k) the number of members of the management board, the functions and responsibilities, term of office, and the condition for their removal;

l) the number of members of the control committee of the company, their functions and responsibilities, and term of office;

m) the main functions and responsibilities, extent of liability of the company's manager and the conditions for his employment and dismissal;

n) the time and manner in which the performance and audit reports of the company are to be presented to the General Assembly;

o) matters related to the relationship between the management and the members of the company or between members of the company;

p) other matters agreed upon by members of the company in accordance with the provisions of this Proclamation.

፲፬. ምዝገባ

፩/ ማንኛውም የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ በዚህ አዋጅ መሰረት ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ፊት ቀርቦ መመዝገብ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) በተደነገገው መሰረት ለመመዝገብ የሚቀርብ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የምዝገባ ማመልከቻ ሲያቀርብ የሚከተሉትን መረጃዎች በማያያዝ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣

14 Registration

1/ Every agribusiness company shall be registered by the Ministry or Appropriate Authority in accordance with this Proclamation.

2/ A company that applies for registration pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall submit the following documents with the application:

a) minutes of the meeting of the founders;

ለ) የመመስረቻ ጽሁፍ ሦስት ቅጂዎች፤

ሐ) የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ስም፣ አድራሻ እና ፊርማ፤

መ) ከሦስት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ዝርዝር የንግድ ስራ እቅድ፤

ሠ) የመነሻ ካፒታሉን መጠንና ተሰብስቦ በባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

ረ) የአደራጅ ኮሚቴ የኦዲት ሪፖርት፤

ሰ) ኩባንያው ሥራውን የሚያካሂድበት ቦታ መግለጫ፤ እና

ሸ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች።

፫/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተዘረዘሩ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባ ሰርተፍኬት ይሰጣል።

፬/ አደራጅ ኮሚቴው ኩባንያውን ማደራጀት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአራት ወራት ውስጥ የማደራጀት ሂደቱን አጠናቆ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ለምዝገባ ማቅረብ አለበት።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በመደራጀት ላይ የሚገኘውን ኩባንያ ማስመዝገብ ካልተቻለ የኩባንያው አባል ለመሆን ድርሻ የገዙ ፈራሚዎች ገንዘባቸው ከነወለዱ ወይም በዓይነት የተደረገ መዋጮ በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ይመለስላቸዋል።

b) three copies of the memorandum of association;

c) names, addresses and signatures of the members of the management board;

d) a detailed business plan covering three to five years;

e) the amount of initial capital and a document confirming its collection and deposit in a bank account;

f) audit report of the Organizing Committee;

g) description of the business places of the company; and

h) other information required in accordance with the Directives issued for implementation of this Proclamation.

3/ The Ministry or Appropriate Authority shall issue a certificate of registration upon confirmation of the fulfillment of the requirements under Sub-Article (2) of this Article.

4/ The organizing committee should complete the formation of the company and submit it to the Ministry or the Appropriate Authority within Four months from the date of commencement of the formation process.

5/ If it is not possible to get the company registered within the time limit prescribed under Sub-Article (4) of this Article, subscribers who have purchased the company's shares shall be refunded their cash payments with interest or have their in-kind payments returned within Thirty working days.

፮/ በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ምዝገባ ያከናወነ ማንኛውም የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ተጨማሪ ምዝገባ ማድረግ ሳያስፈልገው ከተሰማራበት የግብርና እሴት ሰንሰለት ጋር የተገናኙ ሌሎች ስራዎች ሊሰራ ይችላል፡፡

፯/ ኩባንያው ምዝገባውን በየዓመቱ ማሳደስ ይኖርበታል፡፡

፲፭. <u>የኩባንያው ስያሜ፣ የሕግ ሰውነትና የኃላፊነት ወሰን</u>

፩/ ማንኛውም የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ መጠሪያ ስም እና መለያ ምልክት ይኖረዋል፡፡

፪/ የኩባንያው ስም እና መለያ ምልክት ሕግን የማይጥስና የሕዝብን ሞራል የማይቃረን መሆን አለበት፡፡

፫/ ኩባንያው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

፬/ የአባላቱ ኃላፊነት በኩባንያው ውስጥ ባላቸው የድርሻ መጠን ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

፭/ የኩባንያው ኃላፊነት በኩባንያው ሀብት ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

፮/ ከማንኛውም ኩባንያ ስም መጨረሻ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ" የሚል ሐረግ መጨመር ይኖርበታል፡፡

፲፮. <u>የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የስራ መስኮች</u>

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች ከዚህ በታች በተለመከቱት ዋና ዋና ተግባራት ሊሰማሩ ይችላሉ፡-

፩/ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ አግሮኬሚካል፣ የእንስሳት እና ሌሎች የግብርና ግብዓቶችን እና መገልገለያ መሳሪዎችን ማቅረብ፤

6/ Any company legally registered in accordance with this Article may undertake other activities related to its areas of operation along the agricultural value chain without a need for additional registration.

7/ The Company shall renew its registration annually.

15. <u>Name, Legal Personality and Liability of the Company</u>

1/ Every agribusiness company shall have a name and brand mark.

2/ The name and brand mark of the company should not violate the law and contradict with public morals.

3/ The Company shall have legal personality starting from the date of registration.

4/ The liabilities of the members of the company shall be limited solely to their shares in the company.

5/ The liabilities of the Company shall be limited to the assets of the company

6/ The phrase "Limited Agribusiness Company" shall be added at the end of the name of every company.

16. <u>Areas of Business of an Agribusiness Company</u>

Agribusiness companies may be engaged in the following major activities:

1/ Supplying improved seeds, fertilizers, farm equipment, agrochemicals, animal inputs, and other agricultural inputs and equipment;

፪/ የግብርና ምርትና ግብዓቶችን ማምረት፣ ግዥ መፈጸም፣ ማሰባሰብ፣ በደረጃ መለየት፣ ማስተዳደር፣ ገበያ ማፈላለግና ትስስር መፍጠር፣ ምርትና ግብዓቶችን ለሀገር ውስጥና ለዓለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ፤

2/ Producing agricultural products and inputs, purchasing, aggregating, grading, managing, searching for markets and creating linkages, and supplying the products and inputs to domestic and international markets;

፫/ ምርት ማቀነባበር፣ ማከማቸት፣ ሳይበላሽ ማቆየት፣ ማሸግ፣ የምርት ማሸጊያዎችን ማዘጋጀት፣ የገጠር የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም እና ሌሎች የእሴት መጨመር ሥራዎችን ማካሄድ፤

3/ Processing, storing, preserving and packaging products, preparing packaging materials, establishing rural industrial processing plants and undertaking other value addition activities;

፬/ ለሰብል፣ ለእንሰሳት እና ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም እንዲሁም ለመሬት ዝግጅት የሚውሉ የመስኖ፣ የድህረ ምርት፣ የምግብ ማቀነባበሪያዎችና የደን ውጤት ማምረቻ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ማስገባትና ወደ ውጭ መላክ፤

4/ Importing and exporting technologies for crops, livestock, natural resource development and use, land preparation, irrigation and post-harvest, production of forest products and food processing;

፭/ ከኩባንያው የሥራ መስክ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሥልጠና፣ የትምህርት፣ የጥገና፣ የግብርና ኤክስቴንሽን፣ የሙያ ምክርና የእንስሳት ጤና አጠባበቅ አገልግሎቶችን መስጠት፤ የመለዋወጫ ዕቃዎች ማቅረብ፤ ለግብርናና ለገጠር ልማት የሚውሉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን ማምረትና ማቅረብ፤ እንዲሁም ከነዚሁ ሥራዎች ጋር የተያያዙ የጥናትና የልማት ሥራዎችን መሥራት፤

5/ Providing training, education, maintenance, agricultural extension, professional advisory and animal health services relevant to the areas of bussines of the company, supplying spare-parts, producing and supplying technologies suitable for agriculture and rural development, and undertaking related study and development activities;

፮/ መጋዘን፣ ምርት ማሸጊያና ማቀነባበሪያ ፋሲሊቲዎች፣ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎቶችን እንዲሁም ሌሎች የግብርና ሎጂስቲክስ እና መሰረተ ልማት አገልግሎት ማቅረብ፤

6/ Providing warehouse and product packaging and processing facilities, transportation and logistics, and other agricultural logistics and infrastructure services;

፯/ የግብርና ቢዝነስ ስራ ለማሳለጥ የሚያስፈልግ አማራጭ የአነስተኛ ታዳሽ ኃይልን ማመንጨት፣ ማጎልበት፣ ማስተላለፍ ወይም ማሰራጨት፤

7/ Generating, developing, transmitting, or distributing alternative small-scale renewable energy required for facilitating agribusiness operations;

፰/ ለመስኖ፣ ለቤት ውስጥ አገልግሎትና ሌሎች የግብርና ቢዝነስ ስራዎችን ለመስራት የሚያስፈልግ የውሃ ሀብት መለየት፣ ማጎልበት፣ መሰረተ ልማት መዘርጋት፣ ለአገልግሎት ማቅረብ እና ማስተዳደር፤

8/ Identifying, developing, building infrastructure, supplying and administering water resources required for irrigation, domestic use, and other agribusiness activities;

፱/ በአካባቢና ተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም በማሳደግ ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፤

9/ Actively participating in enhancing environmental and natural resource conservation and use;

፲/ የአባላትን የቁጠባ ባህል ለማጎልበት የሚረዳ ግንዛቤ መስጠት፣ የፋይናንስ አቅርቦትና ተደራሽነት ማስፋት፣ የብድር አገልግሎት ማቅረብ እና የኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያድግ ማመቻቸት፤

10/ Creating awareness on culture of saving among its members, expanding the supply and accessibility of financial resources for members of the company, providing credit services and facilitating to increase insurance coverage for members;

፲፩/ በተናጠል ወይም ከአገር ውስጥ ወይም ከወጪ ባለሃብቶች ጋር በጋራ በተለያዩ ከግብርና ጋር ተያያዥነት ባላቸው ኢንቨስትመንቶች መሳተፍ፤

11/ Participating in various investments related to agriculture independently or in collaboration with domestic or foreign investors;

፲፪/ የግብርና መሬት በኢንቨስትመንት፣ በኪራይ ወይም በሊዝ በመወሰድ የማምረት ተግባር ላይ መሳተፍ፤

12/ Undertaking production activities by acquiring agricultural land through investment, lease or rent;

፲፫/ አባላት በተለያዩ ምክንያቶች መሬታቸውን ማልማት ሳይችሉ ሲቀሩ ፈቃደኝነታቸው ላይ ተመስርቶ መሬቱን በውል ተረክቦ ማልማት ወይም ማስተዳደር፤

13/Acquiring land through contract from members who are unable to develop the land for various reasons, and developing and administering the land based on the willingness of and contract with the landholders;

፲፬/ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ግንኙነትና ትብብር መመስረት፡፡

14/ Establishing partnership and cooperation with domestic and international institutions that have similar objectives;

ክፍል ሦስት

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች ሥራ አመራርና አስተዳዳር

፲፯. ጠቅላላ ጉባዔ

፩/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ጠቅላላ ጉባዔ እያንዳንዱ አባል የሚገኝበት የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ የኩባንያው ከፍተኛው አካል ነው።

፪/ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የኩባንያውን የሥራና የሀብት አጠቃቀም ዕቅድና ክንውን መገምገም እና ማጽደቅ፤

ለ) የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ጸሀፊ እና ሌሎች አባላትን መሾም እና መሻር፤

ሐ) የኩባንያውን ሥራ አስኪያጅ በሥራ አመራር ቦርዱ አማካይነት ተወዳድሮ ሲቀርብለት ቅጥሩን ማጽደቅ፤

መ) ኦዲተሮችን መሰየም እና እንደአስፈለጊነቱ ማሰናበት፤

ሠ) የስራ አመራር ቦርድ እና የኦዲተሮችን ሪፖርቶች መገምገም እና ማጽደቅ፤

ረ) ለአባላት የሚሸጠውን የድርሻ ብዛት እና የአንድ ድርሻ ዋጋ መወሰን፤

ሰ) የተጣራ ትርፍ ክፍፍልን መወሰን፤

ሸ) የኩባንያውን የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ማጽደቅ እና አስፈላጊ ሲሆን ማሻሻል፤

SECTION THREE
MANAGEMENT AND ADMINISTRATION OF AGRIBUSINESS COMPANIES

17. General Assembly

1/ The General Assembly of an agribusiness company is the highest body that makes final decisions and constituted by all members of the company.

2/ The General Assembly shall have the following main functions and responsibilities:

a) reviewing and approving the work and asset utilization plans and performance of the company;

b) appointing and dismissing the chairperson, deputy chairperson, secretary and other members of the management board;

c) approve the employment of the company's manager presented by the managenet board following a competitive selection process;

d) appointing and dismissing auditors as deemed necessary;

e) reviewing and approving the reports of the management board and auditors;

f) determining the number of shares to be sold to the members and the price of each share;

g) determining the net profit distribution;

h) approving the company's memorandum of association and internal regulations, and amending the same when deemed necessary;

ቀ) ከሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ጥምረት ወይም ግንኙነትና ትብብር ለመመስረት ውሳኔ መስጠት፤

በ) በስራ አመራር ቦርድ የቀረበለትን የብድር ውል መርምሮ ማጽደቅ፤

ተ) የኩባንያውን መከፈል፣ መዋሃድ ወይም መክሰም በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት፤

ቸ) የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን የሥራ ድርሻ መወሰን፤

ኀ) በኩባንያው ዕቅድ መሠረት የቀረበለትን በጀት መርምሮ ማጽደቅ፡፡

i) making decisions on establishing linkages and cooperation with institutions that have similar objectives which may enable achievement of the company goals;

j) examining and approving loan agreements presented by the management board;

k) making final decision on the division, merger or liquidation of the company;

l) determining the responsibilities of the members of the management board;

m) examining and approving budget in accordance with the company's plan.

፲፰. ስለ ጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ

፩/ ጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይኖሩታል፡፡

፪/ የጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን አጀንዳው በሥራ አመራር ቦርድ ይለያል፡፡

፫/ የጠቅላላ ጉባዔ አስቸኳይ ስብሰባ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊጠራ ይችላል፡-

ሀ) ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት መካከል አንድ ሶስተኛው ስብሰባ እንዲጠራ በጽሁፍ ሲጠይቁ፤

ለ) የስራ አመራር ቦርድ አስቸኳይ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አሉ ብሎ ሲያምን፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) በተደነገገው መሠረት አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ ተጠይቆ የሥራ አመራር ቦርዱ ጥሪ ካላደረገ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለስልጣን ጥሪ እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

18 General Assembly Meeting

1/ The General Assembly shall hold regular and extraordinary meetings.

2/ The regular meeting of the General Assembly shall be held once a year and its agenda shall be determined by the Board of Directors.

3/ An extraordinary meeting of the General Assembly may be convened for the following reasons:

a) When one-third of the General Assembly members request in writing that a meeting be convened;

b) When the Board of Directors deems that there are matters requiring an urgent decision.

4/ Where a request is made to convene an extraordinary general assembly meeting in accordance with Sub-Article (3) pharagraph (a) of this Article, but the management board fails to issue the call, the Ministry or the appropriate

በዚህ ጊዜ ስብሰባው በሥራ አመራር ቦርዱ እንደተጠራ አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ይቆጠራል፡፡

፭/ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚካሄደው፦

ሀ) መደበኛ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ከሆነ ከጠቅላላ አባላቱ ወይም ህጋዊ ተወካዮቻቸው ውስጥ ከግማሽ በላይ ሲገኙ፤

ለ) አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ከሆነ ከጠቅላላ አባላቱ ወይም ሕጋዊ ተወካዮቻቸው ውስጥ ከሁለት ሶስተኛ በላይ ሲገኙ ነው፡፡

፮/ ጠቅላላ ጉባኤ ለማካሄድ ለአባላቱ ሁለት ጊዜ ጥሪ ተደርጎ ምልዓተ-ጉባኤ ካልተሟላ ጉባኤው በሶስተኛ ጊዜ ጥሪ በተገኙት አባላት ይካሄዳል፡፡ ነገር ግን የኩባንያዎች መዋሀድ እና መከፈል የሚመለከቱ ስብሰባዎች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ቢያንስ ሁለት ሦስተኛው አባላት በጉባኤው መገኘት ግዴታ ነው፡፡

፯/ ማንኛውም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ሊካሄድ ከታሰበበት ቀን ቢያንስ ከሰባት ተከታታይ ቀናት በፊት የስብሰባውን አጀንዳ ሰዓትና ቦታ በመግለጽ ለሁሉም አባላት በሚደርስ ሁኔታ ጥሪ ሊተላለፍ ይገባል፡፡

፲፱. ስለ ድምጽ አሰጣጥ

፩/ በአንቀጽ ፵፰ የኩባንያ ውህደትና መከፈል እና በአንቀጽ ፵፱ የኩባንያ መፍረስ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኩባንያው ውሳኔ የሚፀድቀው በአብላጫ ድምፅ ነው፡፡

authority shall cause the call to be issued. In such a case, the meeting shall be deemed an extraordinary general assembly meeting convened by the management board.

5/ A General Assembly meeting shall be held:

a) in the case of a regular General Assembly meeting, when more than half of the total members or their legal representatives are present;

b) in the case of an extraordinary General Assembly meeting, when more than two-thirds of the total members or their legal representatives are present.

6/ Where a quorum is not constituted after two rounds of notice have been issued to the members to hold a meeting of the General Assembly, the meeting shall be held on the third notice with the members present. However, it is mandatory that two-third of the members of the company are present to make decision in meetings regarding merger and division of companies.

7/ Every meeting of the General Assembly shall be notified in the way the call can reach to all members at least seven consecutive days prior to the scheduled date, specifying the agenda, time, and venue of the meeting.

19. Voting

1/ Without prejudice to the provisions stipulated under Article 48 regarding merger and division of company and Article 49 regarding dissolution of company, any decision of the company shall be approved by a majority vote.

፪/ አንድ አባል በኩባንያው ውስጥ ቢያንስ አንድ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አባል ከአንድ በላይ ድምጽ ሊኖረው ይችላል፡፡ የድምጹ ቁጥርም የሚወሰነው ለኩባንያው ባስመዘገበው የመሬት ይዞታ ስፋት እና በሚያቀርበው የምርት መጠን መሰረት ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት በአባሉ የመሬት ይዞታ ስፋት እና በሚያቀርበው የምርት መጠን መሰረት የሚደረገውን የድምጽ ድልድል በተመለከተ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭/ ማንኛውም የኩባንያው አባል በስብሰባ ላይ ተገኝቶ ራሱ ድምፅ መስጠት አለበት፤ ሆኖም የኩባንያው አባላት ቁጥር ከስድስት መቶ በላይ ከሆነ ድምጽ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡ ስለውክልና አሰጣጥ ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፮/ አምራች ድርጅት አባል ሲሆን ድምጽ የሚሰጠው በተወካዩ አማካኝነት ነው፡፡

2/ A member of a company shall have a minimum of One vote.

3/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (2) of this Article, a member may have more than One vote. In such case, the vote shall be determined by the size of land the member registered with the company, and the amount of product he supplies.

4/ The allocation of vote based on the size of land the member registered with the company, and the amount of product he supplies in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall be determined by the Directive to be issued by the Ministry.

5/ Every member of the company should attend the meeting and vote in person; however, if the number of members of the company exceeds six hundred, voting may be cast through delegation. The manner of delegation shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry.

6/ Where a producer organization is a member, it shall cast vote through its representative.

፳. <u>የስራ አመራር ቦርድ አመሰራረት</u>

፩/ የስራ አመራር ቦርድ አባላት ከኩባንያው አባላት በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ በአብላጫ ድምጽ ይመረጣሉ፡፡

፪/ የሥራ አመራር ቦርድ ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡

20. <u>Establishment of the Management Board</u>

1/ The members of management board shall be elected from among the members of the company by a majority vote of the General Assembly.

2/ The management board shall be accountable to the General Assembly.

፫/ የስራ አመራር ቦርድ አባላት ቢያንስ አምስት ቢበዛ ዘጠኝ መሆን አለባቸው፡፡

፬/ ቁጥራቸው የሚፈቅድ አባል ሴቶች በሚገኙበት ማንኛውም የግበርና ቢዝነስ ኩባንያ ውስጥ ሰላሳ ከመቶ አመራር በሴት አባላት መያዝ አለበት፡፡

፭/ ቁጥራቸው የሚፈቅድ አባል ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች በሚገኙበት ማንኛውም የግበርና ቢዝነስ ኩባንያ ውስጥ አስር ከመቶ አመራር በወጣቶችና አካል ጉዳተኞች አባላት መያዝ አለበት፡፡

፮/ የስራ አመራር ቦርድ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሀፊ ይኖሩታል፡፡

፳፩. የሥራ አመራር ቦርድ አባልነት መስፈርቶች

የሥራ-አመራር ቦርድ አባል ለመሆን የሚችለው ቀጥሎ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ አባል ነው፡-

፩/ መልካም ሥነ ምግባር ያለው፤

፪/ ከዚህ በፊት በአደራጅነት፣ በሥራ-አመራር ቦርድ አባልነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ኦዲተርነት ወይም በሌሎች የአመራር ኃላፊነቶች ላይ ተመድቦ ሲሰራ ከኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ በወንጀል ድርጊት ጥፋተኝነቱ ያልተረጋገጠ ፤ እና

፫/ በኩባንያው መመስረቻ ጽሁፍ ወይም በሌላ ሕግ ለቦርድ አባልነት ብቁ የሚያደርጉ ተብለው የተዘረዘሩ ምክኒያቶች፡፡

3/ The members of management board should be at least Five and at most nine.

4/ In every agricultural business company where adequate number of female members are present, thirty percent of the management shall be held by female members.

5/ In every agricultural business company where adequate number of youth and persons with disabilities are present ten percent of the management shall be held by youth and members with disabilities.

6/ The management board shall have a chairperson, a deputy-chairperson, and a secretary to be elected by the General Assembly.

21. Criteria for Membership of the Management Board

A member shall meet the following criteria to qualify for membership of the board:

1/ Be of good moral character;

2/ No record of conviction for committing criminal offenses while serving as a promoter, board member, manager, auditor or holding any other managerial position or under any other circumstance; and

3/ Reasons for competency as specified under the memorandum of association of the company or other laws.

፳፪. <u>የስራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩/ የስራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት በኩባንያው የመመስረቻ ጽሁፍ ይወሰናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቁትን እቅዶችና ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤

ለ) ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት እንዲጸድቅ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

ሐ) አዳዲስ አባላትን ይቀበላል፤

መ) የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ይጠራል፤

ሠ) የኩባንያውን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስጸድቃል፤

ረ) በመመስረቻ ጽሁፍ መሰረት ለአባላት የሚሰጥ የብድር መጠን ይወስናል፤ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ መመለሱን ይከታተላል፤

ሰ) የኩባንያው የፋይናንስ አቅርቦት ዘላቂነትን የሚያረጋግጡ ስራዎችን ይሰራል፤

ሸ) የኩባንያውን ህልውና ሊነዱ የሚችሉ ስጋቶች እንዲለዩ ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ አደጋ የመቀነስ ስትራቴጂ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ቀ) ሌሎች በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ተግባራት ይፈጽማል፡፡

22. <u>Functions and Responsibilities of the Management Board</u>

1/ The functions and responsibilities of the management board shall be determined in the memorandum of association of the company.

2/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, the functions and responsibilities of the management board shall include at least the following:

a) executes the plans and decisions approved by the General Assembly;

b) submits annual work plans and budgets to the general assembly for approval;

c) admits new members;

d) calls meetings of the general assembly;

e) causes preparation of short, medium and long-term strategic plans and submits to the general assembly for approval;

f) determines the amount and provision of loan to the members in accordance with the memorandum of association, and monitors its repayment;

g) undertakes activities that ensure the sustainability of the company's financial supply;

h) identifies risks that could threaten the existence of the company, evaluates them, and implements appropriate risk reduction strategy;

i) Performs other functions assigned by the general assembly.

፳፫. ከሥራ አመራር ቦርድ አባልነት ስለመነሳት

፩/ የሥራ አመራር ቦርድ አባል በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በማንኛውም ጊዜ ከኃላፊነት ሊነሳ ይችላል።

፪/ ማንኛውም የሥራ አመራር ቦርድ አባል በሥራ ዘመኑ ሥልጣኑን ከኩባንያው ጥቅም ጋር በሚጋጭ አኳኋን በመገልገል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያልተገባ ጥቅም ማግኘቱ ወይም ለሌሎች ማስገኘቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ከኃላፊነቱ ሊነሳ ይችላል፡፡

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤው በኩባንያው መመስረቻ ጽሁፍ በሚገለጹት ምክንያቶች የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ሊያሰናብት ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) እና (፫) መሠረት ከሥራ-አመራር ቦርድ አባልነት የተነሳ ሰው ከኃላፊነቱ ከተነሳበት ጊዜ አንስቶ ለሁለት ዓመት በማንኛውም ሁኔታ የኩባንያው ሥራ አመራር ቦርድ አባል መሆን አይችልም፡፡

፳፬. የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ስለመተካት

፩/ የቦርድ አባላት የተጓደሉ እንደሆነ የቀሩት የቦርድ አባላት በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ አለባቸው፤ የተተኪዎቹ አባላት የሥራ ዘመን የሚያበቃው በቀሩት የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን በሚያበቃበት ጊዜ ነው፡፡

23 **Removal from Membership of the Management Board**

1/ A member of the Management Board may be removed at any time by the decision of the General Assembly.

2/ Any member of the Management Board may be removed if it is established that during his term of office the member used his authority in a manner that causes conflict of interests with that of the company and obtained, directly or indirectly, an improper benefit for himself or others.

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) above, the General Assembly may dismiss members of the management Board on grounds specified in the company's memorandum of association.

4/ A person who is removed from membership of the management board pursuant to Sub-Articles (2) and (3) of this Article shall not be eligible under any circumstances to become a member of the company's management board for a period of Two years from the date of removal.

24. Replacing Members of the Management Board

1/ Where there are vacancies in the management board, the remaining board members shall submit the matter to the general assembly within Thirty working days; the term of office of the replaced members shall expire at the same time as the term of office of the remaining board members.

፪/ ሁሉም የቦርድ አባላት ስራቸውን የለቀቁ ከሆነ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ይህ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን መጥራት አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው ተሰብስቦ የቦርድ አባላትን እስኪመርጥ ድረስ የቁጥጥር ኮሚቴው ኩባንያውን ያስተዳድራል፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ የቁጥጥር ኮሚቴው ያከናወናቸው ሥራዎች በውጭ ኦዲተሮች መመርመር አለባቸው፡፡

፳፭. <u>የስራ አመራር ቦርድ አባላት የስራ ዘመን</u>

፩/ የአንድ የስራ አመራር ቦርድ አባል የስራ ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ ለሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን ሊመረጥ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስራ አመራር ቦርድ አባል ሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን ጨርሶ ከተሰናበተ ከአንድ ተጨማሪ የስራ ዘመን በኋላ ዳግም ለመጨረሻ ጊዜ ሊመረጥ ይችላል፡፡

፳፮. <u>የስራ አመራር ቦርድ ስብሰባና ምልዓተ-ጉባኤ</u>

፩/ የስራ አመራር ቦርድ ስብሰባ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ ይካሄዳል፡፡

፪/ ማንኛውም የስራ አመራር ቦርድ ስብሰባ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ አባላት ከተገኙ ይከናወናል፡፡

፫/ የስብሰባው አጀንዳ በሰብሳቢው እና በጸሀፊው ተዘጋጅቶ ቢያንስ ከስብሰባው ሰባት ቀናት አስቀድሞ ለስራ አመራር ቦርድ አባላት መድረስ አለበት፡፡

2/ Where all board members have resigned the members of the Control Committee must call a meeting of the general assembly within thirty working days from the date such event occurred.

3/ The Control Committee shall administer the company until the general assembly convenes and elects board members in accordance with Sub-Article (2) of this Article; the activities carried out by the control committee during this period shall be audited by external auditors.

25. <u>Term of Office of the Members of the Management Board</u>

1/ The term of office of a member of the management board is Three years with the possibility of being reelected for Two consecutive terms.

2/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, a member of the management board who has been dismissed after completing Two consecutive terms may, after an additional term has passed, be re-elected for last term.

26. <u>Meeting and Quorum of the Management Board</u>

1/ Meeting of the management board shall be held at least quarterly.

2/ There shall be quorum for the meeting of the management board if more than half of the members are present.

3/ The agenda for the meeting shall be set by the chairperson and the secretary and shared with the members of management board at least Seven days before the date of meeting.

፳፯. <u>የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ</u>

የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩/ ለስራ አመራር ቦርድ አባላት በተናጠል ወይም በቡድን የስራ ክፍፍል ይሰጣቸዋል፣

፪/ በጠቅላላ ጉባኤ እና በስራ አመራር ቦርድ የተሰጡትን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤

፫/ የኩባንያው አስተዳደራዊ አደረጃጀት የፋይናንስ መግለጫዎቹን እና ቁመናውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆኑን ያረጋግጣል፤

፬/ የቦርዱን ውሳኔ መሰረት በማድረግ የኩባንያውን የአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል በቂ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፭/ ኩባንያው ዕዳውን የመክፈል አቅሙ እየቀነሰ ከሄደ ወይም ዕዳውን መክፈል ካቋረጠ እንደ ሁኔታው ዕዳን መልሶ የማዋቀር ወይም የማደራጀት ወይም የመክሠር ሥነ-ሥርዓት እንዲጀመር ያደርጋል፤

፮/ የቦርዱን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ኩባንያው የዋና ካፒታሉን ሦስት አራተኛ በኪሣራ ሲያጣ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ያደርጋል፤

፯/ የጠቅላላ ጉባኤ እና የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባዎችን ቃለ ጉባኤ፣ የሒሳብ መዝገብ፣ የአባላት እና የሥራ አመራር ቦርድ መዛግብት እንዲሁም ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፤

27. <u>The Chairperson of the Management Board</u>

The chairperson of the Management Board shall have the following main functions and responsibilities:

1/ Assign jobs to the members of management board individually or in group;

2/ Execute decisions made by the general assembly and the management board;

3/ Ensure that the administrative structure of the company enables the control of its financial statements and position;

4/ Establish and implement adequate procedures to control the risk exposure and internal processes of the company;

5/ Initiate a debt restructuring or reorganization, or bankruptcy proceedings in cases where the company's ability to pay debts decreases or it stops paying its debts;

6/ Cause an extraordinary meeting of the general assembly to be called based on the decision of the board, if the company loses Three-Fourth of its main capital due to loss;

7/ Ensure that minutes of the meetings of the general assembly and the management board, accounting records, records of the members and the management board, and other necessary documents are kept properly;

፰/ የፋይናንስ እንቅስቃሴን ያካተተ ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

፱/ በዚህ አዋጅ ወይም በመመስረቻ ጽሁፍ መሠረት የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ ለስራ አመራር ቦርድ አቅርቦ ያስወስናል፤

፲/ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲቋቋምና ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፲፩/ በስራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

8/ Present to the General Assembly annual performance report that include financial activity;

9/ Submitting requests for the meeting of general assembly to the management board for decision in accordance with this Proclamation or the memorandum of association;

10/ Ensure that reserve funds are established and maintained in accordance with the decision of the general assembly;

11/ Performs other responsibilities assigned by the management board.

፳፰. <u>የስራ አመራር ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ</u>

የስራ አመራር ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩/ የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢውን ወክሎ ይሰራል፤

፪/ የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ የሚሰጠውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

28. <u>The Deputy Chairperson of the Management Board</u>

The Deputy Chairperson of the management board shall have the following main functions and responsibilities:

1/ Acts as chairperson of the management board in the absence of the chairperson of the board;

2/ Performs other responsibilities assigned by the chairperson.

፳፱. <u>የስራ አመራር ቦርድ ጸሀፊ</u>

የስራ አመራር ቦርድ ጸሀፊ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩/ ከሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ጋር በመሆን የቦርዱን የስብሳባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

፪/ የኩባንያው መረጃዎችና መዛግብት በአግባቡ ተደራጅተው መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

፫/ የኩባንያውን ሪፖርቶችና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ያቀርባል፤

29. <u>The Secretary of the Management Board</u>

The Secretary of the management board shall have the following main functions and responsibilities:

1/ Sets agenda for the meeting of the management board, in collaboration with the chairperson;

2/ Ensures that the information and records of the company are organized and kept properly;

3/ Submitt company reports and other necessary information to the relevant bodies;

፬/ የጠቅላላ ጉባኤ እና የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባዎችን ያዘጋጃል፤

፭/ በስራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፴. <u>የቁጥጥር ኮሚቴ አመሰራረት</u>

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የቁጥጥር ኮሚቴ አመሰራረት እንደሚከተለው ይሆናል፦

፩/ የኩባንያው የቁጥጥር ኮሚቴ ከኩባንያው አባላት መካከል በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል፤

፪/ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ቁጥር ሦስት ሲሆን ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፤

፫/ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፤

፬/ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በማንኛውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሊሻሩ ይችላሉ፤

፭/ የኩባንያው የቁጥጥር ኮሚቴ አባል የሥራ ዘመኑን ጨርሶ ከተሰናበተ ከአንድ ዓመት በኋላ ዳግም ሊመረጥ ይችላል።

፴፩. <u>የቁጥጥር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የቁጥጥር ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነት ይኖሩታል፦

፩/ የኩባንያውን ገንዘብና ንብረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

፪/ የኩባንያውን ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች በሕግ፣ በኩባንያው መመስረቻ ጽሁፍ እና ውስጠ ደንብ መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላል፤

4/ Organizes the meetings of the general assembly and the management board;

5/ Performs other responsibilities assigned by the management board.

30. <u>Establishment of the Control Committee</u>

The establishment of the control committee of an agribusiness company shall be as follows:

1/ The members of the control committee of the company shall be elected by the general assembly from among the members of the company;

2/ The control committee shall have three members and be accountable to the general assembly;

3/ The term of office of the members of the control committee is three years and no member shall be reelected for more than two consecutive terms;

4/ The members of the control committee may be removed at any time by the decission of the general assembly;

5/ A member of the control committee, who has been dismissed after completing his term, may be re-elected after One year.

31. <u>Functions and Responsibilities of the Control Committee</u>

The Control Committee shall have the following functions and responsibilities:

1/ Controls that the funds and assets of the company are properly utilized;

2) Monitors that the various activities of the company are conducted in accordance with the law, the memorandum of association and internal Regulations of the company;

፫/ በጠቅላላ ጉባኤው ተለይተው የተሰጡትን ውሳኔዎችን ያስፈጽማል፤

፬/ በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፴፪. <u>ስለ ሥራ አስኪያጅ</u>

፩/ የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ቅጥር በሥራ አመራር ቦርድ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤ ይጸድቃል።

፪/ የሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለስራ አመራር ቦርድ ነው።

፫/ የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ሀ) ኩባንያውን ወክሎ ይዋዋላል፤ በፍርድ ቤት ይከራከራል፤

ለ) የኩባንያውን ፋይናንስ ያስተዳድራል፤ ክፍያዎች በወቅቱ መፈጸማቸውን ያረጋጋጣል፤

ሐ) የሒሳብ መዛግብት ለውጪ ኦዲተሮች በአስፈላጊው ጊዜ እንዲቀርቡ ያደርጋል፤

መ) የኩባንኒያውን ጠቅላላ የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል፤ ኩባንያዉን በመወከል ይፈርማል፤

ሠ) የኩባንያውን አቅም ለማሳደግ የሚጠቅሙ አዳዲስ የቢዝነስ ሀሳቦችንና አካሄዶችን ይቀርጻል፤ በስራ አመራር ቦርድ ሲጸድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ) በኩባንያው መመስረቻ ጽሁፍ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፤ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ኩባንያውን ይወክላል፤

ሰ) በሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤ የቦርዱን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤

3/ Executes decisions specifically given by the general assembly;

4/ Performs other functions assigned by the general assembly.

32. <u>The Manager</u>

1/ The employment of the company's manager shall be presented by management board and approved by the General Assembly.

2/ The manager of the company shall be accountable to the management board.

3/ The manager of the company shall have the following functions and responsibilities:

a) enters into agreement on behalf of the company and represents the company at court;

b) administers the financial affairs of the company and ensures that payments are effected duly;

c) makes sure that financial records of the company are presented to external auditors on time;

c) manages day-to-day operations of the company and signs on behalf of the company;

e) formulates new business ideas and approaches useful for enhancing the capacity of the company, and implements them when approved by the management board;

f) represents the company in its relations with third parties, unless there is a contrary provision in the memorandum of association of the company;

g) performs assignments given by the management board, and executes the decisions of the board;

ሸ) የሥራ ዕቅድ እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲጸድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ቀ) የስራ አመራር ቦርዱ ሲፈቅድ ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፤

በ) ሠራተኞች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

ተ) በኩባንያው የመመስረቻ ጽሁፍ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፴፫. <u>የሥራ አስኪያጁ ተጠያቂነት</u>

፩/ በመመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ የተመላከቱ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ በኩባንያው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፪/ ኩባንያው በሥራ አስኪያጁ ውሳኔ አሰጣጥ ምክንያት ለሚደርስበት ኪሳራ የኩባንንያውን ኪሳራ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፴፬. <u>ስራ አስኪያጅን ስለማሰናበት</u>

፩/ የኩባንያውን ሥራ አስኪያጅ የማሰናበት ውሳኔ በኩባንያው ሥራ አመራር ቦርድ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤ ይጸድቃል፡፡

፪/ በተሰናበተው ሥራ አስከያጅ ምትክ ሌላ ስራ አስኪያጅ እስኪቀጠር ድረስ ከኩባንያው ተቀጣሪ ሠራተኞች መካከል አንዱ ወይም የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ተክቶ ይሠራል፡

፫/ በተሰናበተው ሥራ አስከያጅ ምትክ ሌላ ስራ አስኪያጅ እንዲቀጠር የስራ-አመራር ቦርዱ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ማስፀደቅ አለበት፡፡

h) prepares the work plan and budget of the company, submits to the board, and implements when approved;

i) hires and dismisses employees of the company when authorized by the management board;

j) leads and manages employees of the company;

k) performs other functions specified in the memorandum of association of the company.

33. <u>Liabilities of the Manager</u>

1/ The manager shall be liable in accordance with the applicable laws for the damage he causes to the company in violation of the provisions of the memorandum of association.

2/ The manager shall pay any loss incurred by the company due to his manner of decision-making.

34. <u>Dismissal of the Manager</u>

1/ A decision to dismiss the manager shall be presented by the management board and approved by the general assembly.

2/ One of the employees of the company or the chairperson of the management board shall act in place of the dismissed manager until another manager is employed.

3/ The management board shall present a nominee to the general assembly and cause the employement of another manager within Thirty days to replace the dismissed manager.

፴፭. የአማካሪ ቦርድ

፩/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰን የአማካሪ ቦርድ ይኖራቸዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአማካሪ ቦርድ የመክፈል አቅም የሌላቸው፣ በምስረታ ወይም በጅምር ላይ ያሉ፣ ወይም በተደጋጋሚ ኪሳራ የገጠማቸው ኩባንያዎች የአማካሪ ቦርድ እንዲኖራቸው አይገደዱም፡፡

፫/ ኩባንያው የአማካሪ ቦርድ እንዲኖረው ሲታመንበት የቦርዱ አባላት የብቃት መስፈርት፣ ብዛት፣ የሙያ ስብጥር እና ጥቅማጥቅም በጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል፡፡

፬/ የአማካሪ ቦርድ ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፡፡

፭/ የአማካሪ ቦርድ አባላት የኩባንያውን ዓላማ የሚጋሩ፣ ብቃት ያላቸው እና ከኩባንያው ጋር ለመስራት የሚፈልጉ ግለሰቦች ከተለያዩ ተቋማት እንዲሁም ከአካባቢው ማሕበረሰብ ተወካዮች ተጠቁመው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት የተጠቆሙ ግለሰቦች በሥራ አመራር ቦርዱ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤ ይሾማሉ፡፡

፯/ የአማካሪ ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ የሥራ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ አባላት ለተጨማሪ አንድ የስራ ዘመን ብቻ እንደገና ሊሾሙ ይችላሉ፡፡

35. Advisory Board

1/ Agribusiness companies shall have advisory board based on the decision of the general assembly.

2/ Whithout prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, those companies which don't have the capacity to pay for advisory board or which are beginners or have repeatedly suffered losses are not obliged to have an advisory board.

3/ When it is believed that a company should have an advisory board, the criteria for qualification, the number, and composition of qualification and benefits of the members shall be determined by the general assembly.

4/ The advisory board shall be accountable to the general assembly.

5/ Individuals who share the objectives of the company, have the required qualifications, and interested in working with the company may be nominated for membership of the advisory board from various institutions and representatives of local communities.

6/ Individuals who are nominated in accordance with Sub-Article (5) of this Article shall be presented by the management board for appointment by the general assembly.

7/ The term of office of the members of the advisory board shall be Three years with the possibility of reappointment for One additional term.

፴/ የአማካሪ ቦርድ አባላት በዋነኝነት ለስራ አመራር ቦርድ እና ለጠቅላላ ጉባኤው የምክር አግልግሎት መስጠት ሲሆን የአስፈጻሚነት፣ የአስተዳደራዊና ውሳኔ ሰጪነት ሚና አይኖራቸውም፡፡

፴፩/ የኩባንያው አማካሪ ቦርድ አባላት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

ክፍል አራት
ስለ መብትና ግዴታዎች

፴፮. የአባላት መብት

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አባላት የሚከተሉት መብቶች ይኖራቸዋል፡-

፩/ በጠቅላላ ጉባዔ የመሳተፍ፣ ሀሳብ የመስጠት፣ የመምረጥና የመመረጥ፤

፪/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተደነገገው መሰረት አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ የመጠየቅ፤

፫/ የትርፍ ክፍፍል የማግኘት፤

፬/ ድርሻ የመግዛት፣ ለሌሎች አባላት የመሸጥ ወይም ለወራሽ የማስተላለፍ፤

፭/ አስፈላጊውን መስፈርት በማሟላት የግብርና ግብዓትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ የብድር፣ የገበያ፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶችን የማግኘት፤

፮/ የኩባንያውን የስራ እንቅስቃሴ እና አስተዳደር ሁኔታ በተመለከተ መረጃ የማግኘት፤

፯/ ኩባንያው የሚያወጣቸውን አዳዲስ ድርሻዎች የመግዛት፤

8/ The members of the advisory board shall provide advisory services primarily to the management board and to the general assembly, and shall have no executive, administrative, or decision-making roles.

9/ The detailed functions and responsibilities of the members of the Advisory Board of the company, and other related matters shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry.

SECTION FOUR
RIGHTS AND OBLIGATIONS

36. Rights of the Members

The members of an agribusiness company shall have the following rights:

1/ Participating in the general assembly, expressing their opinions, electing and being elected;

2/ Requesting an extraordinary meeting of the general assembly to be called in accordance with Article 18 Sub-Article (3) of this Proclamation;

3/ Getting dividend;

4/ Purchasing shares, selling to other members or transferring to heirs;

5/ Getting supply of agricultural inputs and technologies, credit, marketing, advisory and other services by fulfilling the necessary requirements;

6/ Accessing information regarding the operations and administration of the company;

7/ Purchasing new shares issued by the company;

፰/ ከኩባንያው በሚወጣበት ወቅት በኩባንያው ሕግና ደንብ መሠረት የሚጠበቁለትን መብትና ጥቅሞች የመጠየቅ፡፡

8/ Claiming the rights and benefits to which he is entitled under the company's law and internal regulations upon leaving the company.

፴፯. <u>የአባላት ግዴታዎች</u>

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አባላት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖራቸዋል፡-

37. <u>Obligations of the Members</u>

The members of an agribusiness company shall have the following obligations:

፩/ ከኩባንያው መውጣት ቢፈልግ ከዘጠና ቀናት በፊት ቅድሚያ የማሳወቅ፤

1/ If the member decides to withdraw from the company, providing notice Ninety days prior to the date of withdrawal;

፪/ የኩባንያውን መመስረቻ ጽሁፍ እና በጠቅላላ ጉባኤ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን የማክበር፤

2/ Complying with the memorandum of association of the company and decisions passed by the general assembly;

፫/ የግብርና ምርቶችን በገባው ውል ስምምነት መሰረት የማቅረብ፤

3/ Supplying agricultural products in accordance with the contract signed with the company;

፬/ የኩባንያውን ጥቅም የሚጎዳ የማጭበርበር ወይም ሐቀኝነት የጎደለው ድርጊት አለመፈፀም፣ የኩባንያውን መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፍ ተግባር አለመፈፀም፤

4/ Refraining from engaging in fraudulent and dishonest activities; refraining from acts that cause damage to the good name and reputation of the company;

፭/ የኩባንያውን ሀብት በአግባብ መጠቀም፤ ብድሮችን ወይም ቅጣቶችን በወቅቱ መክፍል፤

5/ Properlly use the assets of the company; paying debts or fines on time;

፮/ የኩባንያውን ሚስጥራዊ የንግድ መረጃዎች ለራሱ ያልተገባ ጥቅም አለማዋል ወይም ለሌላ ሰው አሳልፎ አለመስጠት እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ውስጥ አለመሳተፍ፤

6/ Refraining from making undue use of the commercial secrets of the company for personal benefits or sharing them with others, and other similar activities that harm the interests of the company;

፯/ ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን የማክበር፡፡

7/ Complying with this Proclamations and the Regulations and Directives issued for its implementation.

፴፰. ከአባልነት መሰናበት እና ቅሬታ አቀራረብ

፩/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አባል ከአባልነት ሊሰናበት የሚችለው ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ነው፡-

ሀ) በራሱ ፈቃድ ከኩባንያው ለመሰናበት ጥያቄ ሲያቀርብ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች ባለመወጣት ምክንያት በኩባንያው የሥራ አመራር ቦርድ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባዔው ከኩባንያው እንዲሰናበት ሲወሰን፡፡

፪/ ማንኛውም ከኩባንያው የተሰናበተ አባል የኩባንያው የመመስረቻ ጽሁፍ በሚፈቅደው መሠረት መብቱ ይጠበቅለታል፡፡

፫/ በራሱ ፈቃድ ከአባልነት የተሰናበተ አባል ከአንድ ዓመት በኋላ ወደ ኩባንያው ለመመለስ ጥያቄ ካቀረበ በሥራ አመራር ቦርድ ውሳኔ ሊመለስ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች ባለመወጣቱ በአስተዳደራዊ ቅጣት በጠቅላላ ጉባኤ የተሰናበተ አባል ከተሰናበተበት ከአንድ ዓመት በኋላ ለመመለስ ጥያቄ ካቀረበ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ሊመለስ ይችላል፡፡

፭/ ከኩባንያው ጋር በተያያዘ በወንጀል ጥፋተኝነት ተፈርዶበት ከአባልነት የተሰናበተ አባል ወደ አባልነት ለመመለስ ጥያቄ ካቀረበ የወንጀል ቅጣቱን ከጨረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ወደ አባልነት ሊመለስ ይችላል፡፡

38. Dismissal from Membership and Submission of Complaints

1/ A member of an agribusiness company may be dismissed on One of the following grounds:

a) When a member submits a request to withdraw from the company;

b) When a member breaches the obligations stipulated under Article 37 of this Proclamation, and the general assembly decides to dismiss the member based on a proposal from the management board.

2/ Any member who is dismissed shall have their rights protected in accordance with the memorandum of association of the company.

3/ A member who withdraw from membership may apply to rejoin the company after one year, and may be readmitted by the decision of the management board.

4/ A member who is dismissed due to breach of the obligations stipulated under Article 37 of this Proclamation may be readmitted by the decision of the general assembly if the member applies for readmission after One year.

5/ A member who is dismissed due to conviction for committing a criminal offense related to the company may be readmitted based on the decision of the general assembly if he submits an application for readmission Two years after serving the punishment.

፮/ ማንኛውም አባል በዚህ አዋጅ መሠረት ከአባልነት መሰናበቱ ወይም ሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣቶች የተጣለበት መሆኑ በሌሎች ሕጎች የሚኖርበትን ተጠያቂነት የሚያስቀሩ አይደሉም፡፡

፯/ ማንኛውም አባል የቀረበበትን ክስ የማወቅና ራሱን ለመከላከል የመሰማትና ማስረጃ ለስራ አመራር ቦርድ የማቅረብ መብት አለው፡፡

፰/ ማንኛውም አባል በቀረበበት ክስ ላይ ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ቅሬታ ካለው ለጠቅላላ ጉባኤው የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

6/ The imposition of administrative penalties or dismissal in accordance with this Proclamation do not relieve a member from liabilities under other relevant laws.

7/ Every member shall have the right to know the allegation brought against him, to be heard, and to present evidence in his own defense to the management board.

8/ Every member who has a grievance following a decision made on the allegation brought against him shall have the right to submit the grievance to the General Assembly.

፴፱. <u>የኩባንያው ግዴታ</u>

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖራቸዋል፡-

39. <u>Obligations of the Company</u>

Agribusiness companies shall have the following obligations:

፩/ የተቋቋሙበትን መርህ እና ዓላማ አክብሮ የመስራት፤

1/ Operating with due respect to the principles and objectives of its establishment;

፪/ አባላት የሚፈልጉትን አገልግሎት በተያዘው ዕቅድ መሠረት የማቅረብ፤

2/ Providing the services needed by the members in accordance with plans;

፫/ ለአባላት በየዓመቱ የትርፍ ክፍፍል የማድረግ፤

3/ Distributing dividends to the members annually;

፬/ በሃገሪቱ ሕግ መሠረት ለቀጠራቸው ሠራተኞች መብታቸውን የመጠበቅ፤

4/ Protecting the rights of employees in accordance with the laws of the country;

፭/ ለመንግስት መክፈል የሚገባውን ግብር እና ሌሎች ክፍያዎች በሕጉ መሠረት ወቅቱን ጠብቆ ገቢ የማድረግ፤

5/ Paying taxes and other payments due to the government on time in accordance with the law;

፮/ የመመስረቻ ጽሁፉን፣ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የማክበር፤

6/ Complying with its memorandum of association, this Proclamation and the subsequent Regulations and Directives;

፯/ ለሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ሪፖርት የማቅረብ እና መረጃ የመስጠት፡፡

7/ Providing the necessary information and reports to the concerned bodies.

ክፍል አምስት

ድርሻ ስለሚያስገኛቸው ውጤቶች፣ የትርፍ ክፍፍል እና ስለመጠባበቂያ ገንዘብ

፵. ድርሻ የሚያስገኛቸው ውጤቶች

፩/ እያንዳንዱ ድርሻ ለአባላት ከሚከፋፈል ትርፍ እንዲሁም ኩባንያው ሲፈርስ ከሚቀረው የተጣራ ንብረት ድርሻ የማግኘት መብት ይሰጣል፡፡

፪/ አንድ አባል የሚያገኘው የትርፍ ክፍፍልና ኩባንያው ሲፈርስ ከተጣራው ንብረት የሚያገኘው ድርሻ አባሉ ለኩባንያው የከፈለውን የድርሻ መጠን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡፡

፵፩. ድርሻ ስለማስተላለፍ

፩/ በማንኛውም ምክንያት የሚደረግ የድርሻ ማስተላለፍ በጽሁፍ መሆን አለበት፡፡

፪/ የኩባንያው ድርሻ የሚተላለፈው በአባላት መካከል ብቻ ነው፡፡

፫/ የኩባንያው ድርሻ በአባላት መካከል ያለገደብ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

፬/ የኩባንያው ድርሻ በአባላት መካከል ሲተላለፍ በድርሻ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ በሚገኘው የድርሻ ዋጋ ይሆናል፡፡

፵፪. ድርሻ በውርስ ስለማግኘት

፩/ አንድ አባል በሞት ሲለይ የሚቹ ወራሾች የኩባንያው አባል የመሆን መብት ይኖራቸዋል፡፡

፪/ የሚች ወራሾች የኩባንያው አባል መሆን የማይፈልጉ ከሆነ፡-

ሀ) የወረሱትን ድርሻ በኩባንያው ሕግና ደንብ መሠረት የአባልነት መሥፈርት ለሚያሟላ ሰው ወይም ለኩባንያው በመሸጥ መውጣት፤ ወይም

SECTION FIVE

EFFECTS OF SHARE, DIVIDENDS AND RESERVE FUNDS

40. Effects of Share

1/ Each share entitles the shareholder to the right to receive dividend and share from the remaining net assets in case of dissolution of the company.

2/ The dividends to be received and the share from assets upon dissolution of the company should be proportional to the value of share the member has paid to the company.

41. Transfer of Share

1/ Any transfer of shares for whatever reason should be made in writing.

2/ Shares shall be transferred only between the members of the company.

3/ Shares may be transferred among members without restriction.

4/ The transfer of share among members shall be at the par value of the share as it appears in the records of shares of the company.

42. Acquiring Shares through Inheritance

1/ The heirs of a deceased member shall have the right to become members of the company.

2/ If the heirs of a deceased member do not want to become members of the company, they have the right to:

a) withdraw by selling the shares to a person who meets the membership requirements or to the company in accordance with the laws and internal regulations of the company; or

ለ) በመጨረሻው በኩባንያው ሀብትና ዕዳ መግለጫ መሠረት በኩባንያው ሀብት ውስጥ የሚወክለው የሟቹ ድርሻ ከመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲከፈላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ስር በተመለከተው መሠረት ለወራሾች ለመክፈል ኩባንያው የመጠባበቂያ ገንዘብ ከሌለው ክፍያ ከተጠየቀበት ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከነወለዱ ለመክፈል ዋስትና ይሰጣል፡፡

፵፫. <u>የትርፍ ክፍፍል</u>

፩/ ኩባንያው በዓመቱ ካገኘው የተጣራው ትርፍ ላይ ለመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲሆን የተወሰነው እና በኩባንያው መመስረቻ ጽሁፍ መሠረት ተቀናሽ የሚሆን ገንዘብ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው ለአባላት ይከፋፈላል፡፡

፪/ የትርፍ ክፍፍል የሚደረገው በእያንዳንዱ አባል የድርሻ መጠን፣ ለኩባንያው በሚያቀርበው የምርት መጠን እና በሚጠቀመው አግልግሎት መሠረት ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር ከተደነገጉት የትርፍ ክፍፍል መስፈርቶች ውስጥ የድርሻ መጠን የሚያስገኘው የትርፍ ክፍፍል ድርሻ ከአርባ ከመቶ ማነስ የለበትም፡፡

፬/ ኩባንያው መክሰሩ በኦዲት ሪፖርት ሲረጋገጥ፣ ያገኘው ትርፍ ዝቅተኛ ሲሆን፣ አስቀድሞ የተያዙና ኢንቨስትመንት የሚፈልጉ የስራ እቅዶች ሲኖሩ ወይም ኩባንያው ወደፊት የሚከፍለው እዳ ሲኖር ጠቅላላ ጉባኤው የትርፍ ክፍፍል እንዳይደረግ ሊወስን ይችላል፡፡

b) be paid from the reserve fund the value which the shares of the deceased member represent in the assets of the company based on the final statement of assets and liabilities of the company.

3/ If the company does not have sufficient reserve fund to pay the heirs in accordance with Sub-Article (2) of this Article, it shall provide security to pay the amount with interest within Six months from the date the payment is requested.

43. <u>Dividends</u>

1/ The annual net profit shall be divided among the members of the company after the amount decided for reserve fund and any amount to be deducted in accordance with the memorandum of association are deducted.

2/ The dividend shall be distributed among the members based on the number of shares held by each member, the volume of products the member supplies to the company, and the services used by the member.

3/ From the criteria stipulated under Sub-Article (2) of this Article for distribution of dividend, the amount derived from the number of shares held by each member shall not be less than Fourty percent.

4/ If an audit report confirms loss by the company, the profit amount is low, there are planned investments or there are debts to be paid, the general assembly may decide that the profits not be divided.

፭/ ኩባንያው የተለያዩ ማህበራዊ ኃላፊነቶችን ለመወጣት የሚያስችል ገንዘብ ከመጠባበቂያ ገንዘብ ላይ ተቀናሽ አድርጐ ሊመድብ ይችላል፡፡

፵፬. <u>ስለመጠባበቂያ ገንዘብ</u>

፩/ የኩባንያው መጠባበቂያ ገንዘብ በትርፍና ኪሳራ ሒሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው የተጣራ ትርፍ ላይ አስቀድሞ ተቀንሶ ወደ መጠባበቂያ ገንዘብ ይዘዋወራል፡፡

፪/ የኩባንያው መጠባበቂያ ገንዘብ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ወይም በኩባንያው መመስረቻ ጽሁፍ መሠረት እንዲቀመጥ የተወሰነ መጠባበቂያ ገንዘብ፤

ለ) በመመሪያ ወይም በኩባንያው የመመስረቻ ጽሁፍ መሠረት እንዲቀመጥ ከተወሰነው ውጭ በጠቅላላ ጉባኤው እንዲቀመጥ የተወሰነ የመጠባበቂያ ገንዘብ፡፡

፵፭. <u>ዋና ገንዘብ ስለማሳደግ</u>

፩/ የኩባንያው ጠቅላላ ጉባኤ ሳይፈቅድ የኩባንያውን ዋና ገንዘብ ማሳደግ አይቻልም፡፡

፪/ የኩባንያውን ዋና ገንዘብ ተጨማሪ ድርሻዎች በማውጣት ወይም የነባር ድርሻዎችን ዋጋ በመጨመር ማሳደግ ይቻላል፡፡

፫/ ጠቅላላ ጉባኤው የኩባንያውን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ ሲወስን የሚያድግበትን መንገድም አብሮ መወሰን አለበት፡፡

5/ The company may deduct funds from the reserve fund and allocate to enable it to discharge various social responsibilities.

44. <u>Reserve Fund</u>

1/ The reserve fund of the company shall be deducted in advance from the net profit indicated in the profit and loss statement and transferred to the reserve fund.

2/ The reserve fund shall include the following:

a) the reserve fund amount determined by a Directive issued pursuant to this Proclamation or the memorandum of association of the company;

b) any reserve amount determined by the general assembly, other than the reserve fund fixed by a Directive or the memorandum of association of the company.

45. <u>Increasing Capital</u>

1/ The capital of the company shall not be increased without the approval of the general assembly.

2/ The capital of the company can be increased by issuing new shares or by increasing the par value of the existing shares.

3/ The General Assembly, when deciding to increase the capital of the company, should also decide the method for increasing the capital.

ክፍል ስድስት

መዋሃድ፣ መከፈል እና መፍረስ

፵፮. መዋሃድ

፩/ የሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች ውህደት ኩባንያዎቹ ተቀላቅለው አንዱ ሌላውን ወይም ሌሎቹን በመዋጥ፣ አልያም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ኩባንያዎች አዲስ ኩባንያ በመመስረት ነባር ኩባንያዎቹ በአዲሱ ኩባንያ ውስጥ በመጠቃለል ሊሆን ይችላል፡፡

፪/ አዲስ ኩባንያ በመመስረት በሚደረግ መዋሃድ ጊዜ የሚዋሃዱት የግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች ሙሉ ንብረት እና እዳቸውን አዲስ ወደ ተመሠረተው ኩባንያ ከመተላለፉ በፊት አዲት ተደርገው ይከሰማሉ፡፡ ለከሰሙት ነባር ኩባንያዎች አባላት በአዲሱ ኩባንያ ውስጥ ምትክ ድርሻ ይሰጣቸል፡፡

፫/ አንዱ ኩባንያ በሌላ ኩባንያ በመዋጥ በሚደረግ መዋሃድ ጊዜ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች ሙሉ ንብረት እና እዳ ወደሚውጠው ኩባንያ አዲት ተደርጎ የተዋጠው ኩባንያ ይከሰማል፡፡ ለተዋጡት ኩባንያዎች አባላት በዋጠው ኩባንያ ውስጥ ምትክ ድርሻ ይሰጣቸዋል፡፡

፵፯. መከፈል

፩/ የአንድ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ሙሉ ንብረት እና እዳዎች ከአንድ በላይ ለሆኑ ነባር ወይም አዲስ ለሚመሠረቱ ኩባንያዎች በማከፋፈል አዲት ተደርጎ የሚከፈለው ኩባንያ ሊከስም ይችላል፡፡

SECTION SIX

MERGER, DIVISION AND DISSOLUTION

46. Merger

1/ Merger of two or more agribusiness companies may be either by one of the companies absorbing the rest or two or more agribusiness companies forming a new company and merging into the new one.

2/ In case of a merger through formation of a new company, two or more agribusiness companies transfer all their assets and liabilities to the newly formed company and desolve after the companies are audited. Members of the dissolved companies shall be issued with replacement shares in the new company.

3/ In case of merger through acquisition by an existing company, one or more agribusiness companies transfer all their assets and liabilities to another preexisting company and dissolve after the companies are audited. Members of the dissolved companies shall be issued with replacement shares in the acquiring company.

47. Division

1/ An agribusiness company may be divided by transferring all its assets and liabilities to more than one preexisting or newly formed companies and the divided company dissolves after auditing.

፪/ ወደ ነባር ኩባንያዎች በመጠቅለል በሚደረግ መከፈል የአንድ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ሙሉ ንብረት እና ዕዳዎች ለነባር ኩባንያዎች ተከፋፍለው አዲት ተደርጐ የሚከፈለው ኩባንያ ሊከስም ይችላል፡፡

2/ In case of division through incorporation into existing companies, an agribusiness company dissolves by transferring all its assets and liabilities to more than one preexisting companies after auditing.

፫/ አዲስ ኩባንያ በመመሥረት በሚደረግ መከፈል አንድ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ሁሉንም ንብረትና ዕዳ ራሱ ለመሠረተው አዲስ ኩባንያ በማስተላለፍ አዲት ተደርጐ ሊከስም ይችላል፡፡

3/ In case of a division through the formation of a new company, an agribusiness company dissolves after auditing by transferring all its liabilities and assets to the new company it established.

፬/ የአንድ የተከፈለ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አባላት የተከፈለውን ኩባንያ ንብረትና ዕዳዎች በተከፋፈሉት ኩባንያዎች ውስጥ ምትክ ድርሻ ይሰጣቸዋል፡፡

4/ Members of the company that is divided shall be issued with replacement shares in the companies which acquired the assets and liabilities of the divided company.

፵፰. <u>የውህደት እና መከፈል ውሳኔ</u>

48. <u>Decisions on Merger and Division</u>

፩/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ውህደት ወይም መከፈልን የሚመለከቱ ውሳኔዎች በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ከተገኙት አባላት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲደገፍ ውሳኔው ይጸድቃል፡፡

1/ Decisions regarding merger or division of an agribusiness company shall be approved if it is supported by the vote of Two-Third of the members present at the meeting of the general assembly.

፪/ በኩባንያው ውህደት እና መከፈል ወቅት ንብረት እና እዳዎችን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ከመተላለፋቸው አሰቀድሞ ባለ ሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሀሳቡ ለሁሉም የኩባንያው አባላት እና ገንዘብ ጠያቂዎች በፅሁፍ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡

2/ Decisions regarding merger or division of an agribusiness company should be provided, in writing, to all members and creditors of the company within Thirty consecutive days before the decisions are made.

፫/ በኩባንያው የመመስረቻ ጽሁፍ ወይም በሌላ ውል ውስጥ ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ቢኖር እንኳን፣ የውህደት ወይም የመከፈል ውሳኔን ያልተቀበለ የኩባንያው አባል ወይም ባለገንዘብ ውሳኔውን እንዲያውቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ፡-

3/ Notwithstanding any contrary agreement in the memorandum of association of the company or any other contract, any member or creditor of the company who does not consent to the decision of merger or division may, within Thirty consecutive days from the date of receiving a copy of the decision:

ሀ) የኩባንያው አባል ከሆነ ሌላ የኩባንያው አባል ለሆነ ሰው ወይም ለኩባንያው ድርሻውን በመሸጥ አባልነቱን ማቋረጥ፤ ወይም ድርሻው በኩባንያ ውስጥ የሚወክለው ዋጋ በገንዘብ ተሰልቶ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ይከፈለዋል፤ ወይም

ለ) የኩባንያው ባለገንዘብ ሲሆን ኩባንያው ገንዘቡን እንዲመለስለት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

፬/ በኩባንያው ውህደት ወይም መከፈል ውሳኔ ያልተስማማ አባል ወይም ባለገንዘብ በተሰጠው በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ያለመስማማቱን ሪፖርት ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ውሳኔውን እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡

፭/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተጠቀሰው ሰላሳ ተከታታይ ቀናት ሳይጠናቀቅ የሚሰጥ የውህደት ወይም የመከፈል ውሳኔ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፮/ የኩባንያው ውህደት ወይም መከፈል የሚጸናው የቀድሞው ኩባንያ ምዝገባ ከመዝገብ ሲሰረዝ እና በውህደት ወይም በመከፈል የተፈጠረው ኩባንያ መመዝገቡ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

፯/ የመዋሃድ ወይም የመከፈል ውሳኔ የሚጸድቀበት የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ከመደረጉ ሰላሳ ተከታታይ ቀናት አስቀድሞ የውህደት ወይም የመከፈል እቅድ፣ ሪፖርት፣ የገለልተኛ ገምጋሚ ሪፖርት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎችና ሰነዶች በኩባንያው ዋና መሥሪያ ቤት እና በቅርንጫፎቹ መቀመጥ አለባቸው፡፡

a) if a member of the company, terminate his membership by selling his shares to another member of the company or to the company; or get paid within Six months the value which the shares calculated in terms of money represent in the company; or

b) if a creditor of the company, demand the company to pay the debt.

4/ Any member or creditor of the company who fails to communicate his disagreement within Thirty consecutive days shall be deemed to have accepted the decision.

5/ Decisions regarding merger or division shall not be effective, if they are made before the expiry of the thirty consecutive days period mentioned in Sub-Article (3) of this Article.

6/ The merger or division of a company shall become effective when the registration of the former company is cancelled and the registration of the company created by the merger or division is entered in the register.

7/ The plan, report by independent evaluators, and other relevant information about the merger or division must be kept at the head office and branches of the company for Thirty consecutive days before the general assembly is convened to approve the decision of merger or division.

፹/ በመዋሃዱ ወይም በመከፈሉ ምክኒያት ህልውናውን ያጣ ኩባንያ አባላት በኩባንያው ውስጥ ከነበራቸው ድርሻ ተመጣጣኝ የሆነ ድርሻ መስጠት ባልተቻለ ጊዜ በድርሻቸው ልክ በጥሬ ገንዘብ የማስተካከያ ክፍያ ይከፈላቸዋል።

፵፱. ስለ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ መፍረስ

፩/ ኩባንያው ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት ሊፈርስ ይችላል፦

ሀ) ጠቅላላ ጉባኤ በስብሰባው ከተገኙት አባላት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ የተደገፈ የመፍረስ ውሣኔ ሲያሳልፍ፤

ለ) ኩባንያው እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ሲወሰን፤

ሐ) የኩባንያው አባላት ቁጥር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) ከተወሰነው ቁጥር ዝቅ ካለ እና በዘጠና ተከታታይ ቀናት ውስጥ ሌላ ሰው በአባልነት ካልገባ፤

መ) በሂሳብ ምርመራ ውጤት መሠረት ኩባንያው የከሰረና የኪሳራውም መጠን የኩባንያውን ህልውና የሚያሳጣ መሆኑ በሚኒሰቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን ሲረጋገጥና በጠቅላላ ጉባኤ ሲጸድቅ።

፪/ ኩባንያው እንዲፈርስ ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን የማፍረስ ውሳኔውን ለሚኒሰቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል።

8/ If it is not possible to provide members of the company that ceased to exist due to division or merger with shares proportional to the shares they held in the company, those members shall be paid compensation in cash equal to the value of the shares they couldn't be given.

49. Dissolution of Agribusiness Company

1/ The company may be dissolved for one of the following reasons:

a) when the general assembly of the company makes decision for dissolution supported by the vote of two-third of the members present at the meeting;

b) when a court orders dissolution of the company;

c) if the number of the members of company falls below the number specified in Sub-Article (2) and (3) of Article 6 of this Proclamation and no new members join within ninety consecutive days;

d) when the Ministry or appropriate authority, based on the result of the financial audit of the company, confirms that the company is insolvent to the extent that prevents its continuation, and this is approved by the general assembly.

2/ When the General Assembly decides to dissolve the company for whatsoever reason, it shall notify the Ministry or Appropriate Authority within Seven working days from the date the decision was made.

፶. ሂሣብ አጣሪ ስለመሰየም

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አንድ ኩባንያ እንዲፈርስ ሲወሰን ሚኒሰቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሂሣብ አጣሪ እንዲመድብላቸው ሥልጣን ለተሰጠው አካል ጥያቄ ያቀርባል፡፡

፪/ ሂሣብ አጣሪው እንደተመደበ የኩባንያውን መዛግብት፣ ሰነዶችና ንብረት ተረክቦ ሂሳብ የማጣራት ስራውን ወዲያውኑ ይጀምራል፡፡

፶፩. የሂሣብ አጣሪው ሥልጣንና ተግባር

፩/ የኩባንያው ሂሳብ አጣሪ የኩባንያውን ገንዘብ መሰብሰብ፣ ዕዳዎችን መክፈል፣ ሀብቱ በሙሉ መሸጥ፣ በማንኛውም ጉዳይ ኩባንያውን መወከል፣ በፍርድ ቤት ክርክር የሚያስነሳ ጉዳይ ሲያጋጥም ጠበቃ መወከል ወይም በራሱ በስምምነት ወይም በግልግል ዳኝነት መጨረስ ይችላል፡፡

፪/ ኩባንኒያው ያለው ሀብት ዕዳዎቹን ለመክፈል በቂ እንደማይሆን ከተገመተ ሂሳብ አጣሪው የኩባንያው አባላት ገቢ ያላደረጉት የድርሻ ዋጋ ካለ ማስከፈል ይኖርበታል፡፡

፫/ ኩባንያው ለሁሉም ገንዘብ ጠያቂዎች ያልከፈላቸውን እዳዎች ሳይከፍል ወይም እዳዎቹን ለመከፈል የሚያስፈልገው ገንዘብ በፍርድ ቤት ውሳኔ በባንክ እንዲቀመጥ ሳያደርግ የኩባንያውን ሀብት ለአባላት ማከፋፈል አይችልም፡፡

፶፪. የገንዘብ ጠያቂዎችን ክፍያ ስለመፈጸም

፩/ ስማቸው በሂሳብ መዝገብ ውስጥ ለተመለከተ ገንዘብ ጠያቂዎች ስለኩባንያው መፍረስ በደብዳቤ እንዲያውቁት እና የሚጠይቁትን ገንዘብ ሊያስረዱ የሚችሉ ሰነዶችን እንዲያቀርቡ ይገለጽላቸዋል፡፡

50. Appointment of Liquidators

1/ Where it is decided that a company be dissolved pursuant to Sub-Article (1) of Article 49 of this Proclamation, the Ministry or the Appropriate Authority shall submit a request to the authorized body for the appointment of a liquidator.

2/ Upon appointment, the liquidator shall start the liquidation task immediately after taking possession of the records, documents and assets of the company.

51. Powers and Functions of the Liquidator

1/ The liquidator may sell the assets of the company, represent the company in court, hire a lawyer, settle disputes through agreement or arbitration, collect payments to the company, and pay debts.

2/ If the assets of the company are deemed to be insufficient to pay its debts, the liquidator shall collect any unpaid value of shares from the members.

3/ The liquidator may not divide the assets of the company among the members until all the debts of the company have been paid to the creditors or an amount sufficient for payment of the debts have been deposited in bank in accordance with the decision of the court.

52. Payment to Creditors

1/ Creditors whose names appear in the book of account shall be notified of the dissolution of the company in writing and requested to submit documents proving the amounts they claim.

፪/ ለኩባንያው ገንዘብ ጠያቂዎች የሚደረገው ክፍያ ሂሳብ አጣሪው ሥራውን በጀመረበት ጊዜ ባዘጋጀው የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ መሠረት ይፈጸማል፡፡

፫/ ለገንዘብ ጠያቂዎች የሚፈጸሙ ክፍያዎች እስከሚፈጸሙ ድረስ የመፈጸሚያ ጊዜያቸው ያልደረሰ ወይም አከራካሪ የሆኑ ክፍያዎችን ለመፈጸም የሚያስችል ተመጣጣኝ ገንዘብ በፍርድ ቤት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

፶፫. <u>የመጨረሻ የሃብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ</u>

፩/ ሂሳብ አጣሪው የኩባንያው ዕዳ ከተከፈለ በኋላ ከተረፈው ንብረት ላይ እያንዳንዱ አባል በመቶኛ ምን ያህል ሊደርሰው እንደሚችል የሚያሳይ የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ማዘጋጀት አለበት፡፡

፪/ ሂሳብ አጣሪው የኩባንያው አባላት የድርሻቸውን ዋጋ ሙሉ በሙሉ መክፈላቸውንና ከአባላቱ ጋር የተያያዙ ቀዳሚ መብቶች ካሉ ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተውን የንብረት ክፍፍል ይወስናል፡፡

፫/ ሂሳብ አጣሪው የፈረመበት የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ሚኒሰቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጋር መቀመጥ አለበት፡

፬/ ማንኛውም አባል የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ያለውን ቅሬታ ለፍርድ ቤት ካላቀረበ የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው እንደጸደቀ ይቆጠራል፡፡

፭/ የመጨረሻው የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ከፀደቀ በኋላ ሂሳብ አጣሪው ኩባንያው ከመዝገብ እንዲሰረዝ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2/ Payments to the creditors of the company shall be made in accordance with the statement of assets and liabilities prepared by the liquidator at the beginning of his work as liquidator.

3/ Until the debts to be paid to the creditors are effected, sufficient amount of funds shall be deposited in court to cover the debts of the company which have not yet matured or are disputed.

53. <u>Final Statement of Assets and Liabilities</u>

1/ The liquidator, after the debts of the company are paid, shall prepare a final statement of assets and liabilities showing the percentage of the remaining assets to be received by each member of the company.

2/ The liquidator shall determine the distribution of assets stated under Sub-Article (1) of this Article, taking into account whether the members have fully paid the value of their shares and any preexisting rights associated with the members.

3/ The final statement of assets and liabilities signed by the liquidator shall be deposited with the Ministry or Appropriate Authority.

4/ The final statement of assets and liabilities shall be deemed approved, if no members submit complaint to the court within three months from the date the statement is deposited.

5/ After the final statement of assets and liabilities is approved, the liquidator shall ensure that the company is cancelled from the register.

ክፍል ሰባት
ለግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች የሚደረግ ድጋፍና ማበረታቻ

፶፬. ማበረታቻ

፩/ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ በማንኛውም ጊዜ ከስራው ጋር በተያየዘ የሚያስፈልጉትን ከውጪ የሚገቡ የግብርና ግብዓቶችና ቴክኖሎጂዎች፣ ለእርሻ አልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች እና ለነዚሁ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚውሉ የመለዋወጫ እቃዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች ከታክስ ነጻ ይደረግለታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን እቃዎችና ግብዓቶች ከውጪ ለማስገባት የሚያፈልገው የውጪ ምንዛሬ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

፫/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ አባላት ያመረቱተትን የግብርና ምርት ሲሸጡ ወይም ከኩባንያው በሚያገኙት የትርፍ ክፍፍል ላይ የገቢ ግብር አይከፍሉም፡፡ ሆኖም ኩባንያው ከሚያገኘው ገቢ ላይ በገቢ ግብር አዋጁ መሰረት ግብር ይከፍላል፡፡

፶፭. ድጋፍ

፩/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ለስራ አመራር ቦርድ፣ ለአባላቱ ወይም ለሰራተኞች ከአገር ውስጥና ከውጭ የአቅም ግንባታ ሥልጠና እና የሰለጠነ የሰው ሃይል ድጋፍ ሊያገኝ ይችላል፡፡

፪/ ኩባኒንያው ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማቶችን፣ ተዘዋዋሪ ፈንድ እና ተመሳሳይ የሆኑ ድጋፎችን ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ሊያገኝ ይችላል፡፡

SECTION SEVEN
INCENTIVES AND SUPPORT FOR AGRIBUSINESS COMPANIES

54. Incentives

1/ Agribusiness company shall be exempt at any time from taxes payable on imported agricultural technologies and inputs, vehicles, spare parts for the vehicles and equipment, and construction materials that are necessary for its undertakings.

2/ It shall be given priority in accessing the foreign currency required for importing the items and inputs listed under Sub-Article (1) of this Article.

3/ Members of agribusiness companies shall not pay income tax on the income they earn by selling agricultural products or from dividends. However,the agribusiness companies shall pay income tax on the revenues they make, in accordance with the income tax Proclamation.

55. Support

1/ The management board of an agribusiness company, its members or employees shall be provided with capacity building trainings and the company may be provided with trained manpower from local and abroad.

2/ The company may be provided with the necessary infrastructures, revolving funds and other similar support from the concerned governmental and non-governmental bodies.

፫/ ኩባንያው ከስራው ጋር ለተያየዘ አገልግሎት የሚውል መሬት በምደባ ከክልል እና ከከተማ አስተዳደሮች ያገኛል፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች ድጋፎችን ያገኛል፡፡

ክፍል ስምንት

የአስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

፶፮. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

፩/ በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች መሰረት መስፈርቱን አሟልቶ ለሚቀርብ ኩባንያ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፪/ ለኩባንያው የብድር ፋይናንስ አቅርቦትን ያመቻቻል፤

፫/ የግብርና ግብዓት አቅርቦት በእራሱና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያመቻቻል፤

፬/ ለኩባንያው ሥራ አመራር እና አባላት የክህሎት ሥልጠና ይሰጣል፤

፭/ ጥናት ላይ በመመስረት ኩባንያው ድጎማና ማበረታቻ እንዲያገኝ ያመቻቻል፤

፮/ የኩባንያው ሥራ አመራር እና አባላት ገበያ ተኮር በሆኑ የግብርና ምርቶች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰሩ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

፯/ ኩባንያው በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መስራቱን ይከታተላል፤ ጉድለትም ከተገኘ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

3/ The company shall get land necessary for it operations through allocation by regional states and city administrations.

4/ The companies shall receive other similar supports in accordance with a Directive to be issued by the Ministry.

SECTION EIGHT

FUNCTIONS AND RESPONSIBILITIES OF EXECUTIVE ORGANS

56. Functions and Responsibilities of the Ministry

The Ministry shall have the following functions and responsibilities:

1/ Issue a certificate of registration to the companies that fulfil the criteria required in accordance with this Proclamation and the subsequent Regulations and Directives;

2/ Facilitate access to credit financing for the company;

3/ Facilitate the supply of agricultural inputs independently or in collaboration with relevant stakeholders;

4/ Provide skill trainings for the members and the management board;

5/ Facilitate for the companies to get subsidies and incentives based on studies;

6/ Create awareness and provide advisory services to the management and members of the companies to ensure that they focus on market-oriented agricultural products;

7/ Monitor, supervise and take appropriate measures to ensure that the operations of the companies comply with this proclamation and subsequent regulations and Directives. Details shall be determined by a Directive.

፶፮. <u>አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት</u>

አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

፩/ መስፈርቱን አሚልቶ የሚቀርብ ኩባንያን ይመዘግባል፤ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፪/ የአነስተኛ ይዞታ አምራቾች በግብርና ቢዝነስ ኩባንያ እንዲደራጁ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ የክህሎት ስልጠና ይሰጣል፤ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

፫/ ኩባንያውን ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በማስተሳሰር የብድር አቅርቦትና ዋስትና እንዲያገኝ ያመቻቻል፤

፬/ የኩባንያውን የእለት ተእለት ተግባር ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ የግብርናና ተያያዥነት ያላቸው መሰረተ ልማቶችን በጥናት በተደገፈ መልኩ ድጋፍ ያደርጋል።

<u>ክፍል ዘጠኝ</u>

<u>የግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎች የኦዲት ሥርዓት</u>

፶፯. <u>የውስጥ ኦዲተር</u>

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የውስጥ ኦዲተር፡-

፩/ በኩባንያው መመስረቻ ጽሁፍ መሠረት ይቀጠራል፤

፪/ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፤

፫/ የፋይናንስ መዝገቦችን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤

፬/ የአሠራር ቅልጥፍናን እና ውጤታማነትን ይገመግማል፤

57. <u>Functions and Responsibilities of Appropriate Authority</u>

The Appropriate Authority shall have the functions and responsibilities:

1/ It shall register a company that meets the requirements and issue a certificate of registration;

2/ Raise awareness, and provide skill-based trainings and other necessary support and follow-up to ensure that smallholder producers are organized into agribusiness companies;

3/ Facilitate linkages between agribusiness companies and financial institutions to enable the companies to access credit services;

4/ Provide study based infrastructure and related support necessary to facilitate the daily operations of the agribusiness companies.

<u>SECTION NINE</u>
<u>AUDIT SYSTEM OF AGRIBUSINESS COMPANIES</u>

58. <u>Internal Auditor</u>

The internal auditor of agribusiness companies shall:

1/ Be hired in accordance with the memorandum of association of the company

2/ Be accountable to the general assembly;

3/ Verify the accuracy of financial records;

4/ Evaluate the efficiency and effectiveness of operational procedures;

ሸ/ የኩባንያውን ንብረት ከብክነትና ጥፋት ይጠብቃል፤

ቀ/ ስጋቶችን በማጉላት ድክመቶች እንዲሻሻሉ ምክረ ሃሳብ ይሰጣል፤

በ/ የኩባንያው እቅድ በአግባብ መተግበሩን በሪፖርትና በመስክ ክትትል ያረጋግጣል፤

ተ/ ለሥራ አመራር ቦርድ እና ለጠቅላላው ጉባዔ ገለልተኛ ሪፖርት ያቀርባል፤

ቸ/ ለውጭ ኦዲተር አሰራር እንዲመች በማድረግ ሰነዶች እንዲደራጁ መምከር፤ በምክረ ሃሳቡ መሰረትም መደራጀቱን ይከታተላል፤

ኀ/ የቅድመ-ኦዲት ዕቅድ፣ የመስክ ስራ ምርመራ እና ትንተና ስራዎችን ያከናውናል፤

ነ/ ሥነ ምግባራዊ ልምዶችን እና የመረጃ ጠቋሚ ዘዴዎችን ያስተዋውቃል፤

ኘ በኦዲት ግኝትና ምክረ ሃሳብ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን በመከታተል ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

አ/ የኩባንያውን ምስጢር ይጠብቃል፡፡

፶፱. <u>የውጭ ኦዲተር</u>

የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የውጭ ኦዲተር፡-

ሀ/ በኩባንያው ውስጠ ደንብ እና በመንግስት አሰራር መሰረት ይሰየማል ፤

ለ/ በስራ አመራር ቦርድና በውስጥ ኦዲተር አማካኝነት ሕጋዊ ፈቃድ ያለው በውድድር ተመርጦ በስቅላላ ጉባኤ እንዲጸድቅ ይደረጋል፤

5/ Safeguard the assets of the company from mis use and embezzlement;

6/ Pinpoint potential risks and provide recommendations for improvement of weaknesses;

7/ Verify execution of operational plans of the company through performance reports and field monitoring;

8/ Submit independent report to the management board and the general assembly;

9/ Advise on organizing documents for external audit processes and monitor compliance with such advisory recommendations;

10/ Conduct pre-audit planning, field examinations and analysis;

11/ Promote ethical practices and establish whistleblowing mechanisms;

12/ Monitor the implementation of corrective measures taken based on audit findings and recommendations, and submit to the general assembly;

13/ Be duty bound to maintain the secrets of the company.

59. <u>External Auditor</u>

An external auditor of agribusiness companies shall:

1/ It shall be appointed in accordance with the company's internal regulations and government procedures;

2/ Be selected by the management board and the internal auditor and approved by the general assembly;

፫/ የኦዲት ግኝት ሪፖርቱን ለቅላላ ጉባኤ በጽሁፍ ያቀርባል፤ በአካል በመገኘት የኦዲት ግኝቱን ያብራራል፤

፬/ በሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት የግኝት ሪፖርቱን በተመለከተ ለማብራራት ሲጠየቅ ትብብር ያደርጋል፤

፭ የኩባንያውን ምስጢር ይጠብቃል፡፡

ክፍል አስር
ስለግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የፋይናስ ምንጭ፣ ብድር እና ኢንቨስትመንት

፷. የፋይናንስ ምንጭ

፩/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የውስጥና የውጭ የፋይናንስ ምንጮች ይኖሩታል፡፡

፪/ የኩባንያው የውስጥ የፋይናንስ ምንጮች፡-

ሀ) ከአባላት የሚሰበሰብ ድርሻ ዋጋ፤

ለ) ከምርት ወይም ከአገልግሎት ሽያጭ የተገኘ ትርፍ፤

ሐ) ከኩባንያው ኢንቨስትመንቶች የሚገኝ ትርፍ፤

መ) የኩባንያው መጠባበቂያ ገንዘብ፡፡

፫/ ከውጭ የሚገኝ የፋይናንስ ምንጭ፡-

ሀ) ከፋይናንስ ተቋማት የሚገኝ ብድር፤

ለ) ያለቅድመ ክፍያ ለምርት ማምረቻና ማቀነባበሪያ የሚያገለግሉ የካፒታል ዕቃዎች ለማግኘት አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ፤

ሐ) እንዳስፈላጊነቱ ከመንግስት የሚገኝ ድጎማና ማበረታቻዎች፤

መ) ከልማት ፈንድ የሚገኝ ሃብት፤

ሠ) መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከፋውንዴሽኖች የሚገኙ የፋይናንስ ድጋፎች፡፡

3/ Submit a written report of his findings to the general assembly and shall appear in person to provide clarifications;

4/ Cooperate with relevant government institutions when requested to provide clarifications regarding the audit report;

5/ Be duty bound to maintain the secrets of the company.

SECTION TEN
FINANCIAL SOURCES, CREDIT AND INVESTMENT OF AGRIBUSINESS COMPANIES

60. Sources of Finance

1/ Agribusiness companies shall have internal and external sources of financial resources.

2/ The internal financial sources include:

a) the value of the shares collected from members;

b) profits generated from the sale of products or services;

c) profits obtained from investments of the company;

d) reserve funds of the company.

3/ The external financial sources include:

a) loans from financial institutions;

b) alternative financing options obtained without advance payment for the acquisition of capital goods used in the production and processing;

c) government subsidies and incentives;

d) grants and development funds;

e) contributions from non-governmental organizations and foundations.

፷፩. የብድር አገልግሎት

፩/ ከኩባንያው ተግባራት ጋር በተያያዘ አባላቱ ለሚያከናውኑት ሥራዎች በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ብድር ያመቻቻል፡፡

፪/ የስራ አመራር ቦርዱ ብድር የሚፈቅድበት ሁኔታ፣ የብድር መጠን እና የመመለሻ ጊዜ በኩባንያው የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

፷፪. ኢንቨስትመንት

፩/ ማንኛውም ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ጠቃሚ ሆኖ ሲያገኝ በጠቅላላ ጉባኤ በሚተላለፍ ውሳኔ መሰረት፡-

ሀ) ከሌሎች ኩባንያዎች ድርሻ መግዛት ይችላል፤

ለ) እህት ኩባንያ ማቋቋም፤

ሐ) የእሽሙር ማህበር ድርሻ መግዛት፤

መ) ከማንኛውም ህጋዊ ኩባንያ ጋር ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት ማድረግ ይችላል፡፡

፪/ በዚሁ አንቀጽ መሰረት የሚደረጉ የኢንቨስትምንት ስምምነቶች ዝርዝር መረጃዎች ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ መዝገብ መመዘገብና ለሚኒስትሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ሪፖርት መደረግ አለባቸው፡፡

፫/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ሊመዘገቡ የሚገባቸው ሰነዶች ዝርዝር በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሳናል፡፡

61. Credit Services

1/ The companies shall facilitate for the members of the company to access credits in kind or cash for their activities related to the functions of the company.

2/ The conditions for credit approval by the management board, amount of the credit and repayemnent schedule shall be determined by the internal Regulations of the company.

62. Investment

1/ In order to achieve its corporate objectives, an agribusiness company may, based on the decisions of the general assembly:

a) purchase shares in other companies;

b) establish subsidiary company;

c) purchase shares in joint ventures;

d) enter into investment agreements with any legal corporate entity.

2/ Detailed records of investment agreements entered into pursuant this Article shall be maintained in a dedicated register and reported to the Ministry or Appropriate Authority.

3/ The particulars to be recorded under Sub-Article (2) of this Article shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry.

ክፍል አስራ አንድ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፷፫. ወደ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ስለመለወጥ

ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው የአነስተኛ ይዞታ አምራቾች ድርጅቶች በፈቃዳቸው ወደ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ስፈልጉ በሚከተሉትን ሁኔታዎች ስያሚለ ሊለወጡ ይችላሉ፡-

፩/ ማንኛውም ሕጋዊ ሰውነት ያለው የአነስተኛ ይዞታ አምራቾች ድርጅት በአባላቱ አብላጫ ድምጽ ውሳኔ መመስረቻ ጽሁፉን በማሻሻል ወደ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ መለወጥ ይችላል፤

፪/ የአነስተኛ ይዞታ አምራቾች ሕጋዊ ድርጅቶች ወደ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የመለወጥ ውሳኔያቸውን ለሚኒሰቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፤

፫/ የአነስተኛ ይዞታ አምራቾች ሕጋዊ ድርጅቶች ወደ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ሲለወጡ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ይሆንባቸዋል፤

፬/ ወደ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ለመለወጥ ያልተስማሙ አባላት ድርሻቸውን ለኩባንያው ሽጠው የመውጣት መብት አላቸው።

፷፬. የግንዘብ ጠያቂዎች መብት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፫ መሰረት የአነስተኛ ይዞታ አምራቾች ሕጋዊ ድርጅት ወደ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ሲለወጥ የነባሩ ድርጅት መብትና ግዴታዎች የአዲሱ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የመመስረቻ ጽሁፍ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ለዚሁ ኩባንያ ይተላለፋሉ።

SECTION ELEVEN

MISCELLANEOUS PROVISIONS

63. Conversion to Agribusiness Company

Other organizations of smallholder producers possessing legal personality may voluntarily transform into agribusiness companies, provided they meet the following conditions:

1/ Any organization of Smallholder producers that has legal personality may be voluntarily converted to agribusiness company by amending its memorandum of association by majority vote of their members;

2/ Smallholder producer organizations must notify the Ministry or the relevant authority in writing of their decision to transform into agribusiness companies;

3/ This Proclamation shall apply to legal entities of smallholder producers when they transform into agribusiness companies;

4/ Members who do not agree to the conversion into an agricultural business company have the right to sell their shares to the company and withdraw.

64. Rights of Creditors

1/ When organizations of smallholder producers is converted to agribusiness company in accordance with Article 63 of this Proclamation, all rights and obligations of the preexisting organization shall be transferred to the new agribusiness company effective

from the date the memorandum of association of the new agribusiness company is registered.

፪/ የአዲሱ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የመመስረቻ ጽሁፍ እንደተመዘገበ ወዲያውኑ የነባሩ ድርጅት ገንዘብ ጠያቂዎች ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ ቅሬታ ካላቀረቡ ኩባንያው ዕዳ ከፋያቸው መሆኑ በደብዳቤ ይገለጽላቸዋል፡፡

2/ Upon the registration of the memorandum of association of the new agribusiness company the creditors of the preexisting organization shall be immediately nitified in writing to present evidence for their claims. Unless they lodge complaint, they shall be notified in writing that the company is the debtor for their claims.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ለተቃወሙ ገንዘብ ጠያቂዎች አዲሱ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ይከፍላል፤ ገንዘባቸውን መክፈል የማይችል ከሆነ በቂ ዋስትና የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3/ The new agribusiness company shall settle the claims of creditors who oppose the conversion pursuant to Sub-Article (2) of this Article or have an obligation to provide security if it is unable to pay immediately.

፬/ የአዲሱ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የነባሩን ድርጅት መለወጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲገለፅ ያደርጋል፡፡

4/ The manager of the new agribusiness company shall ensure that the notice of conversion is published in a newspaper of wide circulation.

፷፭. <u>ስለአስተዳደራዊ እርምጃ</u>

65. <u>Administrative Measure</u>

፩/ ይህንን አዋጅ፣ አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ተላልፈው በሚገኙ ኩባንያዎች እና የኩባንያ አመራር አካላት ላይ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን አስተዳደራዊ ማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፡ ዝርዝር አፈጻጸሙም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

1/ The Ministry or the Appropriate Authority shall take administrative corrective measures against companies and company management bodies that are found to be in violation of this Proclamation and the Regulations and Directives issued for its implementation. The details of the implementation shall be determined by a Regulation issued by the Council of Ministers.

፪/ የኩባንያው ሠራተኞች ለሚፈጽሙት ጥፋት አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድበትን የውስጠ ደንብ ኩባንያዎች ያወጣሉ፡፡

2/ The Companies shall issue internal Regulations for taking administrative measures againist the offenses commited by the employees of the company.

፷፮. ስለ ሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

ሌሎች የመንግስት አሰፈጻሚ አካላትና ድርጅቶችን የሚመለከቱ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች፣ ልማዶችና አሠራሮች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

66. Applicability of Other Laws

Without prejudice to other laws governing government executive bodies and organizations, any laws, practices, and procedures that are inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation.

፷፯. የመመስረቻ ጽሁፍ ስለማሻሻል

፩/ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ መመስረቻ ጽሁፍ ሊሻሻል የሚችለው በኩባንያው ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ነው፡፡

፪/ የጠቅላላ ጉባኤው የመመስረቻ ጽሁፉን የማሻሻል ውሳኔ የሚጸድቀው በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ከተገኙ አባላት በሦስት አራተኛ ድምጽ ከተደገፈ ብቻ ነው፡፡

፫/ የመመስረቻ ጽሁፍ በዚህ አንቀፅ መሠረት ከተሻሻለ የማሻሻል ውሳኔው የተላለፈበት ቃለ ጉባኤ ኮፒ ግብርና ቢዝነስ ኩባንያዎችን ለመመዝገብ እና ለማስተዳደር ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርቦ በሰላሳ ቀናት ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

67. Amendment of Memorandum of Association

1/ The memorandum of association may only be amended in accordance with a decision passed by the general assembly.

2/ The decision to amend the memorandum of association shall be approved only if it is supported by the vote of Three-Fourth of the members present at the meeting.

3/ If the memorandum of association is amended in accordance with this Article, a copy of the minutes of the meeting of the general assembly where the decision was passed should be registered within thirty days with the body authorized to register and administer agribusiness companies.

፷፰. አለመግባባት ስለመፍታት

፩/ ማንኛውም ከግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ምስረታ፣ የሥራ አመራርና እንቅስቃሴ ወይም ከመብት እና ግዴታዎች ጋር በተገናኘ የሚነሳ ክርክር ተከራካሪ ወገኖቹ ጉዳዩን በግልግል ወይም በዕርቅ ለመጨረስ በጽሁፍ ስምምነት ላይ ከደረሱ በአዋጅ ቁጥር ፭ሺ፪፻፴፯/፪ሺ፲፫ መሠረት በግልግል ዳኝነት ወይም በዕርቅ ይፈታል፡፡

68. Dispute Resolution

1/ Any dispute in connection with the formation, management, or operation of an agribusiness company shall be settled by arbitration or conciliation in accordance with Proclamation No. 1237/2021, provided that the parties to the dispute have entered into a written agreement to resolve the matter through arbitration or conciliation.

፪/ ማንኛውም የሚነሳው ክርክር በግልግል ወይም በእርቅ የሚፈታው የክርክሩ ጭብጥ መጠኑ በግልጽ ከታወቀ የገንዘብ ዕዳ ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ ወይም ጥያቄው በዋና ተበዳሪው ላይ የሚቀርብ የዋስትና ግዴታን የሚመለከት ከሆነ፣ አሊያም በውሉ መሠረት መቅረብ የነበረበት ምርት ባለመቅረቡ ምክንያት የሚነሳ የውል መጣስ ክርክር ሲሆን ብቻ ይሆናል፡፡

2/ The resolution of a dispute shall be subject to arbitration or conciliation proceedings only where the dispute pertains to liquidated debt, a guarantee claims against a principal debtor, or a claim arising from the non-delivery of products.

፫/ ከዚህ በላይ በተገለጸው መልኩ በግልግል ዳኝነት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው አካል በአዋጅ ቁጥር ፭ሺ፪፻፴፯/፪ሺ፲፫ አንቀፅ ፵፱ መሠረት በፌደራል ደረጃ ሲሆን ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ በክልል ሲሆን ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

3/ Any party aggrieved by an arbitral award rendered pursuant to this Article may in accordance with Article 49 of Proclamation No. 1237/2021, lodge an appeal to the Federal First Instance Court, if the matter arises at federal level, or to the Regional High Court, if the matter arises in a regional state.

፷፱. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

69. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>

፩/ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ The Ministry may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and the Regulations issued pursuant to this Proclamation.

፸. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

70. <u>Effective Date</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

This Proclamation shall enter into force as of the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ፯ኑሜ ፫ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

Done at Addis Ababa, On this 8th day of September 2026

ታዬ አፅቀሥላሴ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

TAYE ATSKESELASSIE
PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA